# አስተምህሮተ ቤተክርስቲያን

# (Ecclesiology)

**ኮርስ ኮድ A5**

www.holisticbiblecollege.com

ሆሊስቲክ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ

2012 ዓ.ም

*ይህንን ማስተማሪያ ሞጁል ያለ ኮሌጁ ፈቃድ ማባዛት የተከለከለ ነው።*

***© Copy Right Holistic Bible College 2012***

***All Rights Reserved***

**ሌሎች ኮርሶችን መማር የምትፈልጉ**

**E-mail፡-** infohbc2017@gmail.com

**P.O.B፡-** 997 **Call፡-** +251919741700/ 0118206642/ +251961416796

**Website፡-** www.holisticbiblecollege.com

**E-Learning፡-** www.holisticbiblecollege.org

**Facebook፡-** Holistic Bible College

**Telegram፡-** @HolisticBibleCollege ወይም http፡//t.HolisticBibleCollege

**Address፡-**

-Tsebay Buildg, Autobus Tera 7th Floor (Addis Abeba)

-Awash Buildg, 2nd Floor, Piassa, (Hawassa)

www.holisticbiblecollege.org

# ማውጫ


መግቢያ ..... 3

የኮርሱ ዓላማ ..... 4

ምዕራፍ 1 ቤተክርስቲያን ..... 5

1.1 ቤተክርስቲያን ምንድናት? ..... 6

1.2 የቤተክርስቲያን ስዕላዊ መገለጫዎች ..... 12

1.3 የቤተክርስቲያን ሥልጣን ..... 17

1.4 የቤተክርስቲያን አገልግሎት ..... 19

1.5 የቤተክርስቲያን አስተዳደር ..... 23

ማጠቃለያ ..... 25

የክለሳ ጥያቄ አንድ ..... 27

ምዕራፍ 2 የቤተ ክርስቲያን ገጽታዎች እና መለያዎች ..... 29

2.1 የቤተክርስቲያን ገጽታዎች ..... 31

2.2 የአጥቢያ ቤተክርስቲያን የጊዜ ቀመር ..... 34

2.3 የቤተክርስቲያን መለያዎች ..... 35

ማጠቃለያ ..... 37

የክለሳ ጥያቄ ሁለት ..... 38

ምዕራፍ 3 የቤተክርስቲያን ስርዓቶች ..... 41

3.1 የውሃ ጥምቀት ..... 42

3.2 የጌታ እራት ..... 47

3.3 ልዩ ልዩ ስርዓቶች ..... 52

ማጠቃለያ ..... 54

የክለሳ ጥያቄ ሦስት ..... 55

የክለሳ ጥያቄዎች መልስ ..... 58

ዋቢ መጽሐፍት ..... 59


www.holisticbiblecollege.org

# መግቢያ

ስለ ቤተክርስቲያን ስናስብ በርካታ አመለካከቶች ይነገራሉ እንዲሁም የተለያዩ አመለካከቶች ይንጸባረቃሉ፡፡ በዚህ ማስተማርያ ሞጁል የተወሰኑ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን በመዳሰስ ስለ ቤተክርስቲያን ያለንን አመለካከት እናሰፋለን፡፡

ቤተክርስቲያንን በተመለከተ በልምድ ብዙ ዓይነት አመለካከቶችና ትርጉሞች ይሰጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ ትክክለኛውን ትርጉም፣ የቤተክርስቲያን ቅድመ ሁኔታ፣ የእግዚአብሔር ዓላማ ቤተክርስቲያን ምን እንደሆችና በማን እንደተመሰረተች ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረቱ ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ቃልስ ምን ይላል? የሚሉ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ይኖርብናል፡፡

ስለዚህ ይህን መሰረት በማድረግ ቤተክርስቲያን ምንድን ናት? የማን ናት? እነማንን ታካትታለች? በምድር ላይ ያላት ዓላማስ ምንድነው? የሚሉ በጣም አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በማተኮር መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ እውነቶችን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

www.holisticbiblecollege.org

# የኮርሱ ዓላማ

የአስተምህሮተ ቤተክርስቲያን ኮርስ ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. የቤተክርስቲያንን እውነተኛ ማንነት ማወቅ፤
2. የቤተክርስቲያን ገጽታዎችን መረዳት፤
3. የቤተክርስቲያን አስተዳደር ስርዓቶችን መረዳት፤
4. ጌታ ኢየሱስ ለቤተክርስቲያን የሰጣትን ዋና ዋና ስርዓቶችን መረዳት ነው።

www.holisticbiblecollege.org

# ምዕራፍ 1 ቤተክርስቲያን

ማውጫ

| ክፍል | መታወቅ ያለበት |
|---|---|
| 1.1 ቤተክርስቲያን ምንድናት? | • ቤተክርስቲያን ምን እንዳልሆነ እና ምን እንደሆነች መረዳት። |
| 1.2 የቤተክርስቲያን ስዕላዊ መገለጫዎች | • የቤተክርስቲያን ስዕላዊ መገለጫዎችን ጥቀስ። |
| 1.3 የቤተክርስቲያን ሥልጣን | • የቤተክርስቲያን ሥልጣን ምንድነው።<br>• የስነ-ስርዓት እርምጃ ዓላማ ምንድነው። |
| 1.4 የቤተክርስቲያን አገልግሎት | • የቤተክርስቲያን የውስጥ እና የውጭ አገልግሎት ምንድነው።<br>• ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ ትምህርት ምን ሊሆን ይገባል። |
| 1.5 የቤተክርስቲያን አስተዳደር | • ጳጳሳዊ አስተዳደር ምንድነው።<br>• ማሕበረ ምዕመናዊ አስተዳደር ምንድነው።<br>• ሽማግሌያዊ አስተዳደር ምንድነው።<br>• ጥምር አስተዳደር አስተዳደር ምንድነው። |

www.holisticbible

# 1.1 ቤተክርስቲያን ምንድናት?

ለአሁኑ ዘመን የቤተ ክርስቲያንን ምንነት በተለያየ መልኩና አንዳንዴም

ለእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይጣጣም ትርጉመ ወሰን ሲሰጠው ስለምናይ ይህንን

ቀብ ማየታችን የበለጠ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ምንድነች? ወይም

ጥነው? ቤተ ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል "ቤተ ክርስቲያን" መሆኗን

የሚገልፁ ነገሮች ምንድን ናቸው? "የክርስቶስ አካል" የሚለው ምንን ያጠቃልላል?

ሱም የአካሉ፥ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው።" የሚለውን ሐሳብ እንዴት

እንረዳው ይገባል? የሚሉትን ጥያቄዎች በጥሞና ልናያቸው ይገባል፡፡

www.holisticbiblecollege.org

ለበርካታ ዓመታት ስለ ቤተ ክርስቲያን ጉዳይ ልዩ ጥናት ያደረገው የፉለር

ተሎጂካል ሰሚናሪ ፕሮፌሰር የሆነው ቻርለስ ቫን ኢንገን ቤተ ክርስቲያንን እንዲ

፧ ብሎ ይተረጉማታል፦ "ቤተ ክርስቲያን ማለት አንድነትን፥ ቅድስናን፤ እርቅንና

ካልን የክርስቶስን ማንነት በሚያንጸባርቅ መልኩ የምታውጅ ናት፡፡ ከዚህ

ሳብ በመነሣት የሚከተሉትን ሐሳቦች ማንሣት እንችላለን።

1. አንዲት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሕያውነቷን ለመግለፅ እነዚህ አራት መግለጫ

ሻ ሊኖራት ይገባል፡- የልብ፥ የአፍና የሐሳብ አንድነት (ሮሜ 15፡5-6)፤ ቅድስና

1:7፣ 1ቆሮ. 1:2)፣ እርቅ (ኤፌ. 4:25-32) ወንጌላችን የሆነውን በፍጹም

ዓዊነቱና በፍጹም መለኮታዊ ባሕርያቱ ማወጅና ማብሠር (ሮሜ 1:1-4)፡፡

2. "የክርስቶስ አካል" የሚለው ሐሳብ ቤተ ክርስቲያንን ወይም የአማኞች ሕብረ

ትን፤ ወይም አዲሱ የክርስቶስ ሕብረተ ሰብን እንጂ (ኤፌ 2፡11-22)፣ ክርስቶስን አያመለክትም፡፡ በቆላስይስ 1፡18 ላይ "እርሱም የአካሉ ማለትም የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው።" በሚልበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያንና ክርስቶስን አንዱ/ እኩል (equate) ማድረጉ አይደለም። ስለዚህ ኣካሉ ክርስቶስ አይደለም፤ ይልቁንም ክርስቶስ ከቤተ ክርስቲያን በላይና ያለፈ (above and beyond) ነው። የቤተ ክርስቲያን ኣውራና ባለቤትም እርሱ ራሱ ነው! (ቆላ. 2፡17)

3. ቤተ ክርስቲያን ድርጅት (institution) አይደለችም፡ ምንም እንኳን መደራጀት ቢያስፈልጋትም፡፡

4. ቤተ ክርስቲያን የሙት ባሕር (static) አይደለችም፡ ሕይወት ያላትና ሕይወት ንም የምታመነጭ (Dynamic) ናት እንጂ፡፡

5. ቤተ ክርስቲያን የምንሰበሰብበት ሕንጻም ኣይደለችም፡ ምንም እንኳን ሕንጻው ለጌታ የተቀደሰ የተለየ ቢሆንም፡፡ ቤተ መቅደሱ ግን እኛ ነን፡ ታቦቱም ክርስቶስ ነው። (1ቆሮ. 3፡16-17፥ 6፡19-20)

6. ቤተ ክርስቲያን ግለሰብ (ፓስተር) + ወይም ግለሰቦች የቤተ ክርስቲያን ሽማግ ሌዎችን ወይንም ደግሞ የፓስተሩና የሽማግሌዎች ጥምርም አይደለችም፡፡ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ አምኖ የዳነው የክርስቶስ አካል የሆነው የእግዚአብሔር ሕዝብ | ነው። የቤተ ክርስቲያን ፓስተር፡ ወይም ሽማግሌዎች፥ ወይንም ደግሞ የፓስተርና የሽማግሌዎች ጉባዔ የክርስቶስን አካል ወክለው ያገለግላሉ፥ ይወስናሉም፡፡

7. በመጨረሻም የማትታየዋ ቤተ ክርስቲያን (INVISIBLE CHURCH) በዓለም

www.holisticbiblecollege.org

አንድ ናት' በክርስቶስ ደም ታጥበው በእርሱ ያመኑና የዳኑ እውነተኛ የአማኞች ስብስብ ናት፡፡ የምትታየው ቤተ ክርስቲያን ግን በየአገሩና በየዜጋው የምትገኝ አጥ ቢያ ቤተ ክርስቲያን ማለታችን ነው። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ድብልቅ ሕዝብ ያለባትና የተሰባጠረ የእምነት ዕድገት ደረጃ ያለው ሕዝብ አቅፋ የምታስተናግድ ናት፡፡

ቤተክርስቲያን ምንድናት የሚለውን ከማየታችን በፊት ምን እንዳልሆነች ማወቅ አለብን። ቤተክርስቲያን ምን እንዳልሆነች ስናውቅ ምንድናት የሚለውን ለማወቅ አንቸገርም።

## ➢ ቤተክርስቲያን ምን አይደለችም?

- ቤተክርስቲያን 500 እና 1000 ሰዎች በስምምነት የሚመሰርቷት የንግድ ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አይደለችም።
- ቤተክርስቲያን በመሰለኝ እና ደስ አለኝ የምትከፈት ሱቅ ሳትሆን የምትተከል ሕያው የክርስቶስ አካል ናት።
- ቤተክርስቲያን የጸሎት ስፍራ ሳትሆን የሚጸልዩ ቅዱሳን ስብስብ ናት።
- ቤተክርስቲያን ገቢ መሰብሰቢያ ኑሮ መደጎሚያ አዲስ የስራ በር መክፈቻ አይደለችም። ቤተክርስቲያን በፓስተር ሆነ በሊቀ ጳጳስ ወይም በንጉስ የምትሰራ ምድራዊ ድርጅት አይደለችም።

## ➢ ቤተክርስቲያን ምንድናት?

- በተለምዶ ቤተክርስቲያን ማለት በጥሬ ቃሉ የክርስቲያን ቤትን ወይም የጸሎት ቤትን ወይም የክርስቲያኖች መሰብሰቢያን ሊያመለክት ይችላል። መንፈሳዊ አተረጓጎሙ ግን ከዚህ ለየት ያለ ነው። ቤተክርስቲያን የተባለው የአዲስ ኪዳን ቃል "ኤክሌሲያ" የሚለው ሲሆን በሰፊው ትርጉሙ ማናቸውም ተጠርተው የወጡ ወይም ጉባዔ ማለት ነው (ሐዋ 7፡38፣ 19፡ 32/41)። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎሙ ደግሞ ቤተክርስቲያን ማለት የአማኞች ጉባዔ ወይም ኅብረት ማለት ነው (1ኛ ቆሮ 1፡2፣ ገላ 1፡13)። ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ የተጠራች የቅዱሳን ጉባኤ እንጂ ግዑዝ ህንጻ አይደለችም። ቤተክርስቲያን የሚሰገድለት ግዑዝ ህንጻ ሳትሆን በመንፈስና በእውነት ለእግዚአብሔር የሚሰግዱ ቅዱሳን ናቸው።

* ሊቀ ጳጳስ አባ መልከ ጼዴቅ *"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እምነትና ትምህርት"* በሚለው መጽሐፋቸው *"ህንጻውን ቤተክርስቲያን እንላለን እንጂ ቤተክርስቲያን ማለት ክርስቶስ በደሙ የዋጃት የመሰረታት እንዲሁም እርሱ ራሱ የሆነላት የምዕመናን አንድነት ማለት ነው። ቤተክርስቲያን የተባል ን እኛ ስንሆን የቤተክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርቶስ ነው"* ብለዋል።
* ቤተክርስቲያን ስንል ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ስራ አምነው ከኃጢአት እስራት ነጻ በመውጣት በኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ስር ሆነው ሁለት ወይም ሦስት ከዚያም በላይ እርሱን ለማምለክ የተሰበሰቡ የአማኞችን ሕብረት ያመለክታል (ማቴ 18፡20፣ ሐዋ 2፡41-47፣ 4፡ 4፣ 13፡1)። ስለዚህም ቤተክርስቲያን ስንል አማኞችን እንጂ ህንፃን አያመለክትም።
* *"በቆሮንቶስ ላለቾ ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን...።"* (1ኛ ቆሮ 1፡1) ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ናት ማንም አገልጋይ "የእኔ ቸርች ናት" ሊል አይገባም። ደግሞም የእኔ ናት ማለት አይችልም።
* ቤተክርስቲያን የእኔም፣ የእኛም ናት አይባልም። የእኔ ቤተክርስቲያን ማለት የምችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። *"እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።"* (ማቴ 16፡18) ከዚህ ክፍል መረዳት የምንችለው የቤተክርስቲያን ባለቤትና መስራች ኢየሱስ እንደሆነ ነው።
* በምድራችን መስራችና ባለ ራዕይ የሚሉት በልምድ ተቀባብለው እንጂ ምንም የመጽሐፍ ቅዱስ መሰረት ላይ ቆመው አይደለም። የቤተክርስቲያን መስራቿም ባለ ራዕዩዋም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አገልጋዮች ባላደራዎችና ተካዮች እንጂ መስራቾች ወይም ባለቤቶች አይደሉም። የቤተ ክርስቲያን መሥራች እና ጀማሪዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተዋጀች በመንፈስ ቅዱስ ለቤዛ ቀን የታተመች በቃሉና በመንፈሱ እየነጻችና እየታነጸች የምትገሰግስ ሠራዊት ናት።

*ይህን ያውቃሉ?*

በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አስተምህሮና ቀኖና መሰረት ቤተክርስቲያን ለመትከል ጽላት/ታቦት ወሳኝ ነገር ነው።

በካቶሊክ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ መሰረት ቤተክርስቲያን ለመትከል በሊቀ ጳጳሳቱ የተሾመ ካህን ያስፈልጋል።

በወንጌላዊያን አስተምህሮ መሰረት ቤተክርስቲያን ለመትከል ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች በቃሉ ዙሪያ መሰባሰብ አለባቸው።

www.holisticbiblecollege.org

- ስለ ቤተክርስቲያን የበለጠውን ለመረዳት በማቴዎስ ወንጌል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸውን እውነቶች እንመልከት። *"... ጌታ ኢየሱስ ቤተክርስቲያኔን እሰራለሁ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም"* (ማቴ 16፡18) አለ። ይህም የሚያመለክተው፡-

✓ ቤተክርስቲያንን የመሰረተው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን፤

✓ ቤተክርስቲያን የጌታ እንደሆነች፤

✓ በማናቸውም የጠላት ተግዳሮቶች ማለትም በማይታየው ዓለም ኃይላት ጥቃት የማትበገር መሆንዋንና ከጌታ ዘንድ ኃይል የታጠቀች መሆንዋን ይገልፃል።

- **ማቴ 18፡15-18 ያንብቡ፡-**
- በዚህ ክፍል ውስጥ በክርስቲያኑ ማህበረሰብ መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ችግሩን ለመፍታት ከቤተክርስቲያን ሥልጣን በላይ ሌላ እንደሌለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን እውነት እንመለከታለን። ችግሩ ለመፍታትም አማኞች በምን መልኩ መስራት እንዳለባቸው የእርቅ ደረጃዎችን በማስቀመጥ ያስረዳል።

✓ ወንድምህ ቢበድልህ አንተ እና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው፤

✓ ባይሰማህ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው፤

✓ እርሱን ባይሰማ ለቤተክርስቲያን ንገር፤

✓ ቤተክርስቲያንን ባይሰማ እንደ አህዛብ እንደቀረጥ ሰብሳቢ ቁጠረው።

- *"ወደ ኢየሩሳሌምም በደረሱ ጊዜ <u>ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያት</u> ሽማግሌዎችም <u>ተቀበሉአቸው፥</u> እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ አወሩ።"* (ሐዋ 15፡5) ከአንጾኪያ ቤተክርስቲያን የመጡ እንግዶችን ከተቀበሉት ውስጥ ቤተክቲስቲያን ተጠሷል። የተቀበለው ሕንጻ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አተረጓጎሙ ቤተ ክርስቲያን ማለት የአማኞች ጉባዔ ወይም ኅብረት ማለት ነው(1ኛ ቆሮ 1፡2)። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን ከእግዚአብሔር መንፈስ ዳግም የተወለዱ አማኞች ሁሉ በሚገኙባትና የኢየሱስ ክርስቶስ አካል በሆነች በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አለች።
- *"የክርስቶስ ኢየሱስ እስር ጳውሎስ ወንድሙም ጢሞቴዎስ፥ ለተወደደውና አብሮን ለሚሠራ ለፊልሞና፥ ለእኅታችንም ለአፍብያ፥ ከእኛም ጋር አብሮ ወታደር ለሆነ ለአርክጳ፥ <u>በቤትህም ላለች ቤተ ክርስቲያን።"</u>* (ቆላ 4፡15) ቤተክርስቲያን ማለት ህንጻው ሳይሆን አማኞቹ ናቸው(ገላ 1፡13)።

www.holisticbiblecollege.org

- ዳግም በተወለዱና መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው በኖረ አማኞች የተሰራችው ይህች ቤተክርስቲያን የምትባለው አካል የተወለደችው ወይም የተመሰረተችው በበዓለ ኀምሳ ቀን ነው(ሐዋ 2፡1-4፣ 37-42)።
- “ቤተ ክርስቲያን” የሚለው ቃል ትርጉም የክርስቲያን ወገን ወይም የክርስቲያን ማኅበረሰብ ማለት ሲሆን ቃሉ በቁሙ ሲወስድ ሕንጻን የሚያመለክት ቢመስልም በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ ግን ቤተ ክርስቲያን ማለት ማህበረ ክርስቶስ ናት።
- ቤተክርስቲያን በክርስቶስ የተገለጠው የወንጌል እውነት ላይ የቆመች ይህንኑ የመዳን ወንጌል ለዓለም ሁሉ ልታውጅ በሕይወቷም ልትገልጸው የተጠራች ባለ ተልእኮ ማኅበረሰብ እንደሆነችና ቤተ ክርስቲያን አገልግሎቷን በትህትናና በቅንነት እንዲሁም በተገቢው ሥርዓት ማከናወን አለባት።
- ቤተክርስቲያን በመንፈስ አንድነት የምትመላለስ የጌታ እራትና የውሃ ጥምቀት በሚባሉ ቅዱሳት ሥርዐቶች አንድነቷን እየገለጸች የቤተክርስቲያን ራስ ከሆነው ከክርስቶስ በተቀበለችው ሥልጣን፤ ምዕመኗን እያስተዳደረችና እየመራች በዓለም ከሚገኝ ዕድፍ ራሷን እየጠበቀችና በጎ ምግባርን እያበረታታች እስከ ጌታ መምጣት ድረስ በዚህ ምድር የምትቆይ የክርስቶስ አካል ናት።

www.holisticbiblecollege.org

# 1.2 የቤተክርስቲያን ስዕላዊ መገለጫዎች

ቤተክርስቲያን ምንና ማን መሆንዋን የበለጠ እንድንረዳ በተለይም ከክርስቶስ ጋር ያላትን ግንኙነት ለማብራራት መጽሐፍ ቅዱስ ስዕላዊ መግለጫዎችን በመጠቀም ይገልጣታል። እነዚህ መግለጫዎች ዋና ዓላማቸው የቤተክርስቲያንና የክርስቶስን ግንኙነት ለማሳየት ነው። እነዚህም ግንኙነቶች የተገለጡባቸው መግለጫዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. **ራስና አካል፡-**

- *"እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ ከሙታንም በኵር ነው።"* (ቆላ 1፡18)
- *"በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ"* (ኤፌ. 4፡4)
- *"ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል።"* (ኤፌ. 5፡30)
- *"በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን።"* (ሮሜ. 12፡4-5)
- ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ቤተክርስቲያን ደግሞ አካል እንደመሆኑ መጠን ራስ የሆነውን ክርስቶስን መታዘዝ፣ በደስታ ማገልገልና መተባበር ይገባታል። አማኞች በአካል መመሰላቸው እያንዳንዱ አማኝ ብልት መሆኑን የሚያመለክት ነው። እያንዳንዱ ብልት ልዩ ልዩ ቢሆንም ማንም ከማንም አይሻልም። አንዱ ደግሞ ከሌላው መለየት የለበትም(1ኛ ቆሮ. 12፡12-13)።
- ጌታ ኢየሱስ የቤተክርስቲያን ራስ ሲሆን ቤተክርስቲያን ደግሞ አካሉ ናት (ኤፌ 1፡22-23፣ ቆላ 2፡19)። አካሉ የሆነች ቤተክርስቲያን ልክ ሰውነታችን ብዙ ብልቶች በአንድ አካል ውስጥ እንዳሉ ሁሉ እንዲሁ ነው (1ኛ ቆሮ 12፡12-27)።

www.holisticbiblecollege.org

- በሰውነታችን ያሉ ሁሉም ብልቶች እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ድርሻ እንዳላቸው ሁሉ በመንፈሳዊ አካልም ብልቶች እያንዳንዳቸው የራሳቸው የሆነ ኃላፊነት አላቸው(ሮሜ 12፡4-8)።
- ስለዚህ የተሳካ ስራ ለመስራት ሁሉም ብልቶች በመተሳሰብና በመደጋገፍ መስራት ይጠበቅባቸዋል፣ የአካል ህልውናው ብልቶች በተገቢው ቦታቸው ስራቸውን በሚገባ መስጠት ሲችሉ ነውና (1ኛ ቆሮ 12፡26)።

**2. ሙሽራና ሙሽሪት፡-**



- *"ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ። እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤ ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለምና፥ ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን፥ ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዳደረገላት፥ ይመግበዋል ይከባከበውማል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።"* (ኤፌ. 5፡25-32)
- *"በእግዚአብሔር ቅንዓት እቀናላችኋለሁና፥ እንደ ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ ወንድ አጭቻችኋለሁና"* (2ኛ ቆሮ. 11፡2)።
- ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የሚኖረው ግንኙነት እንደ ባልና ሚስት እንደተገለጸ እንመለከታለን (ኢሳ 54፡1-8)። በአዲስ ኪዳንም ጌታ ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን ሙሽሪት ብሎ እንደጠራትና (ማር 2፡18-20) ሐዋርያው ጳውሎስም ቤተክርስቲያን እንደ ንፅህት ድንግል ለጌታ የታጨች እንደሆነች ገልጿል (2ኛ ቆሮ 11፡2-3)።
- ስለዚህ ቤተክርስቲያን እንደ ሙሽሪት የከበረ ነገር ስለሚጠብቃት፤ የከበረ ነገር እንደሚጠብቃት በመገንዘብ (1ኛ ቆሮ 2፡9) ተዘጋጅታ የሙሽራዋን የኢየሱስን መገለጥ መጠባበቅ ይኖርባታል (ቲቶ 2፡11-14፣ 1ኛ ዮሐ 3፡2-3)።

www.holisticbiblecollege.org

- ከዚህ ምሳሌ እንደምንረዳው ሙሽራው ወይም ባል የሆነው ክርስቶስ ሲሆን ሙሽሪት ወይም በሚስት የተመሰለችው ደግሞ ቤተክርስቲያን ናት። ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንዴት ያለ ገደብ እንዳፈቀረ እንረዳለን። ቤተክርስቲያን ደግሞ ለዚህ ፍቅር ምላሽ ለመስጠት ንጹህ መሆንና መታዘዝ እንደሚገባት መረዳት እንችላለን(ራዕ. 21፡9)።

**3. ግንድና ቅርንጫፍ፡-**



- *"<u>እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤</u> ገበሬውም አባቴ ነው። ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል። እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ፤ በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም። <u>እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ።</u> ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል" (ዮሐ. 15፡1-5)።*

- ከዚህ ግሩም ምንባብ እንደምንረዳው ክርስቶስ ተሸካሚው ግንድ ሲሆን ቤተክርስቲያን ወይም አማኞች ደግሞ ቅርንጫፎች ናቸው።

**4. እረኛና መንጋ፡-**



- *"መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ ያኖራል።"* (ዮሐ. 10፡11)
- *"በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ያወጣው የሰላም አምላክ።"* (ዕብ. 13፡20)
- *"በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት"* (1ኛ ጴጥ. 5፡2)
- ክርስቶስ ለነፍሱ ሳይሳሳ በሞት ያዳናት የቤተክርስቲያን እረኛ ነው። ቤተክርስቲያንም የእረኛዋን ድምጽ መስማትና እርሱን መከተል ይጠበቅባታል።

**5. ማዕዘን ራስ ድንጋይና ሕያዋን ድንጋዮች፡-**

- *"በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠና ክቡር ወደ ሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችሁ፥ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፥*

www.holisticbiblecollege.org

*በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።"* (1ኛ ጴጥ. 2፡4-5)



- *"እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም። በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል።"* (ኤፌ. 2፡19-22)
- *"... እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።"* (1ኛ ቆሮ 12:13)
- ህንጻ የሚለው ስዕላዊ መግለጫ አማኞች ከጌታ ኢየሱስ ጋርና እንደነርሱ ከሆኑት ከሌሎች አማኞች ጋር ያላቸውን የጠበቀ ግንኙነት ያሳያል (1ኛ ቆሮ 3፡16-17፣ ኤፌ 2፡19-22)።
- ሐዋርያው ጳውሎስ ቤተክርስቲያንን እንደ ህንፃ ሲመስላት ህንጻው የተሰራባቸው ድንጋዮች እያንዳንዱ ምዕመን እንደሆኑ እና የማዕዝኑ ድንጋይ ደግሞ ጌታ ኢየሱስ መሆኑን በመግለጽ ሲሆን ሁሉም ለመንፈሳዊ ስራ እጅግ አስፈላጊ እንደሆኑ (ኤፌ 2፡21) ያስረዳል። በአጠቃላይ ሁሉም ምዕመናን የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ሆነው ይሰራሉ። በተናጠል ደግሞ እያንዳንዱ ምዕመን የመንፈስ ቅዱስ ማደርያ ወይም ቤተመቅደስ ናቸው(1ኛ ቆሮ 6:19)።
- ክርስቶስ የህንጻው መሠረትና የማዕዘኑ ድንጋይ ነው፤ ሕንጻው ደግሞ የተሰራው በአማኞች ሁሉ ነው። እያንዳንዱ አማኝ እንደ ድንጋይ ይመሰላል። እያንዳንዱ ድንጋይ ደግሞ ለህንጻው አስፈላጊ እንደመሆኑ እያንዳንዱም አማኝ በቤተክርስቲያን ውስጥ አስፈላጊ ነው። ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ በቀር በሌላ በማንም በምንም ላይ መመስረት አይገባትም። የማዕዘን ራስ ማለት የህንጻ የርዝመት፣ የወርድና የከፍታ አቅጣጫዎች የሚመሰረቱበት ዋና ድንጋይ ማለት ነው። እንግዲህ ቤተክርስቲያን የምትመሰልባቸው እነዚህ ምሳሌዎች የአማኙንና የምዕመንን ግንኙነት የሚያመለክቱ አመልካቾች ጭምር ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ምሳሌዎች የክርስቶስን ማንነትና የአማኙን ሙብትና ኃላፊነቶችም ያሳያሉ።

በቀድሞይቱ ቤተክርስቲያን ጌታ ኢየሱስ ሲከተሉ የነበሩ ምዕመናንም በተለያዩ ስሞች ይጠሩ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት እንችላለን። ለምሳሌ፡-

- ➢ አማኞች(ሐዋ 4፡32)፡- የዳኑት በሕይወትም የሚኖሩት በእምነት ስለሆነ ይህ ስም ተሰጥቷቸው ይጠሩበታል።

www.holisticbiblecollege.org

- ክርስቲያኖች(ሐዋ 11፡26)፡- የክርስቶስ ተከታዮች ስለሆኑ ከአይሁድ ህዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ ስም ነው።
- ወንድሞች(ሐዋ 11፡29)፡- የአንድ አባት ልጆች ስለሆኑ እና በክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን እድል ስለተሰጣቸው።
- ቅዱሳን(ሐዋ 9፡13)፡- ለእግዚአብሔር የተለየ ወገን ስለሆኑ እና በክርስቶስ ስለተቀደሱ።
- የተመረጡ(ማር 13፡27)፡- እግዚአብሔር የመረጠው የደህንነት መንገድ ማለትም ጌታ ኢየሱስን በማመን የዳኑ ስለሆነ ነው።

## ቤተክርስቲያን በዚህ ምድር መቼ ተጀመረች?

ትክክለኛው የቤተክርስቲያን መጀመሪያ የበዓለ ሃምሳ ዕለት መሆኑን የሚከተሉት ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ።

- ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ 16፡18 ቤተ ክርስቲያን ወደፊት እንደምትመሠረት ተናግሮአል። ይህ በብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያን እንዳልነበረች ያሳያል።
- የክርስቶስ ትንሳኤና ዕርገት ለክርስቲያን ተግባራዊነት አስፈላጊ ነበሩ። ቤተክርስቲያን የተመሰረተቸው በትንሳኤው ላይ ነው (ኤፌ 1፡19-20)። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችም ለቤተ-ክርስቲያን አገልግሎት እንቅስቃሴ እጅግ አስፈላጊ መሳሪያዎች ናቸው። ስለዚህ ክርስቶስ እነዚህን ስጦታዎች ለቤተክርስቲያን ለመላክ ማረግ ነበረበት(ኤፌ 4፡7-12፣ ዮሐ 16፡123)።
- የቤተ-ክርስቲያን ጅማሬ የበዓለ አምሳ ቀን መሆኑን የሚያረጋግጥልን ሌላው ነገር የመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ስራ ነው። ጌታ ከማረጉ በፊት ስለመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አመልክቷል (ሐዋ. 1፡5)። ይኸውም በበዓለ ሃምሳ ዕለት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ተከናወነ ወደ ክርስቶስ አካል ለመግባት ብቸኛው መንገድ የመንፈስ ቅዱስ የማጥመቅ ስራ ስለሆነ ይህ ቀን ትክክለኛ የቤተክርስቲያን ጅምር ነው ወደሚለው ድምዳሜ ልንደርስ እንችላለን።

www.holisticbiblecollege.org

# 1.3 የቤተክርስቲያን ሥልጣን

ቤተክርስቲያን ራሷ ከሆነው ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ የተሰጣትን ተልዕኮ ማለትም ወንጌልን ላለልዳኑት የማድረስና አምነው የዳኑትንም ክርስቶስን ወደ መምሰል የማሳደግ /ደቀመዝሙር/ የማድረግ ኃላፊነት በአግባቡ መፈጸም እንድትችል በሰማይም በምድርም ሙሉ ሥልጣን ያለው ጌታ ራሱ ሥልጣን ሰጥቷታል (ማቴ 28፡ 19-20)።

ለመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን የተሰጣት ሥልጣን ለዛሬዋም ቤተክርስቲያንም የተሰጠ ሥልጣን ነውና ልትጠቀምበት ይገባታል። ይህም ሥልጣን፡-

1. **የዲያቢሎስ እና የሰራዊቱን ስራ ለማፍረስ**

- *"አሥራ ሁለቱንም ሐዋርያት በአንድነት ወደ እርሱ ጠርቶ በአጋንንት ሁሉ ላይ ደዌንም ይፈውሱ ዘንድ ኃይልና ሥልጣን ሰጣቸው።"* (ሉቃ 9፡1)
- ዲያቢሎስ የእግዚአብሔር ስራ እንዳይሰራ በተለያየ መልኩ ቤተክርስቲያንን ይገዳደራል። የማያምኑ ሰዎችን ሀሳብ በማሳወር (2ኛ ቆሮ 4፡4) እንዲሁም አማኞች እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ ሕይወትና አገልግሎት እንዳይመላለሱ በተለያየ መልኩ ይፈታተናቸዋል (1ኛ ተሰ 2፡18)።
- ከጌታ የተነሳ ድል የአማኞች ነው (ማቴ 16፡18-19)። ወንጌል በሥልጣን እንዲሰበክና ምዕመናንም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ይረዳል።

2. **ነፍሳትን ለማትረፍ እና ለመመለስ**

- ጤና በሌለው መንገድ የሚሄዱትን ስንገስጽ ወይም ዲስፕሊን እርምጃ ስንወስድ የዋሆችን በነውራቸው እንዳይሰቡ እንጠብቅበታለን።

3. **እንደ እግዚአብሔር ቃል የስነ-ስርዓት እርምጃ መውሰድ**

- ቤተክርስቲያን የምዕመኗ ሕይወት ለማነጽና በቅድስና ለመጠበቅ እግዚአብሔርን በማያስከብር ሕይወት የሚመላለሱትን መምከርና መገሰጽ ከጥፋታቸው መመለስ ይጠበቅባታል።
- ከጥፋታቸው የማይመለሱ ካሉ ደግሞ የስነ-ስርዓት እርምጃ በመውሰድ እንደ በደላቸው ዓይነትና መጠን የመቅጣትና የማግለል ስልጣን አላት (ማቴ 18፡15-18፣ 1ኛ ቆሮ 5፡1-5)።
- በጥፋተኛው ላይ እርምጃ በመውሰድ የእግዚአብሔርን ጉባዔ ከዓለም የፍርድ አይን መጠበቅ ነው(2ኛ ቆሮ 7፡11፣ 2ኛ ጢሞ 3፡16)። ቅዱሳን በስነ-ስርአቱ አማካኝነት በጌታ መንገድ ይሰለጥናሉ፣ ለቃሉም መታዘዝን ይማራሉ።

**ይህ የስነ-ስርአት እርምጃ ዓላማ፡-**

- የእግዚአብሔርን ክብር ለመጠበቅ ነው፡፡
- በጉባኤ መካከል ነውር እንዲወገድ ካልተደረገ የእግዚአብሔር ስምን ከማቃለል ጋር ተገናኝ ነው፡፡
- የእኛ ድርጊት እግዚአብሔርን ካላከበረ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ሊቃለል ይጀምራል፡፡

www.holisticbiblecollege.org

# 1.4 የቤተክርስቲያን አገልግሎት

ጌታ ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን ሲመሰርታትና በዚህም ምድር ላይ ሕያው ሆና እንድትኖር ሲያደርግ በዓላማ ሲሆን ይህም ፈቃዱንና ሃሳቡን በማገልገል አብራ እንድሰትራ ነው (1ኛ ቆሮ 3፡9)።

የቤተክርስቲያን አገልግሎት ዓይነቶች የውስጥና የውጭ በመባል የሚታወቁ ሲሆን ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን።

➢ <u>**የውስጥ አገልግሎት**</u>

የውስጥ አገልግሎት ማለት የክርስቶስን አካል ለማነጽ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለአማኞች የሚደረገውን አገልግሎት የሚያመለክት ነው። ዓላማው ደግሞ እግዚአብሔርን ማክበር፣ ምዕመናንን ማነጽና መቀደስ ሲሆን በአመራር አገልግሎትና በሁሉም ምዕመናን አገልግሎት የሚፈጸም ነው።

*የውስጥ አገልግሎትም ሊፈጸም የሚችለው፡-*

**1. አምልኮ**

አምልኮ ማለት እግዚአብሔርን መፍራት ወይም ማክበር ማለት ነው። እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ማምለክ የሚችልበትን አቅም ሰጥቶ ነው። ለዚህም ነው ሰዎች ሁሉ የሆነ ነገርን ማምለክ የሚፈልጉት። ይሁን እንጂ ሰዎች እግዚአብሔርን በትክክል አውቀውት በእውነትና በመንፈስ (ዮሐ 4፡24) ሊያመልኩት ይገባል።

የጥንቷ ቤተክርስቲያንም እውነተኛ አምልኮ እንደነበራት ከእግዚአብሔር ቃል መረዳት እንችላለን (ፊል 3፡3)። አማኞች እግዚአብሔርን ማምለክ ያለባቸው ስለማንነቱና ስላደረገላቸው ሁሉ መሆን አለበት። አማኞች መስዋዕት በማቅረብ እግዚአብሔርን ማምለክ እንዳለባቸው የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳናል።

ይህም፡-

- ራሳቸውን ሕያውና ቅዱስ መስዋዕት አድርገው በማቅረብ- ሮሜ 12፡1
- በምስጋና- ዕብ 13፡15
- በዝማሬ- ቆላ 3፡16

www.holisticbiblecollege.org

- እግዚአብሔር በሰጣቸው ገንዘብ ማለትም በአስራት፣ በመባና በስጦታ (ሚል 3፡8-10፣ ዘሌ 27፡30-31) ወዘተ ሊሆን ይችላል።

**2. ጸሎት**

ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ሲሆን የጥንቷ ቤተክርስቲያን የምትታወቅበት አንዱ ልምዷም ይህ ነበር።

ይህም ጸሎት ይደረግ የነበረው በተለያየ ምክንያቶች ነበር፡-

- ወንጌል ለመስበክ ድፍረትን ለማግኘት (ሐዋ 4፡23)፤
- በተለያየ ችግር ውስጥ ስላሉ አማኞችና አገልጋዮች (ሐዋ 12፡5)፤
- አዳዲስ አብያተክርስቲያናት እንዲበረቱ (ሐዋ 14፡24)፤
- ስለታመሙ ሰዎች (ያዕ 5፡16)፤
- የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመረዳት (ሐዋ 6፡1-6)፤
- ለአገልጋዮች የቃሉን መገለጥ እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው(ኤፌ 6፡19-20) ወዘተ ነበር። ስለዚህ አማኞች ስለራሳቸው ይሁን ስለሌሎች ሳያቋርጡ መጸለይ ይጠበቅባቸዋል (1ኛ ተሰ 5፡17)።

www.holisticbiblecollege.org

**3. አስተምህሮ**

አስተምህሮ(ትምህርት) ለጥንቷ ቤተክርስቲያን አንዱ ስራዋ ነበር(ሐዋ 2፡42-47)። ምክንያቱም ያለ መንፈሳዊ ትምህርት አማኞች በሕይወታቸው ማደግ እንደማይችሉ መሪዎችዋ ያውቁ ስለነበር ነው።

ስለዚህ አማኞች የእግዚአብሔር ቃል ተምረው ከሕይወታቸው ጋር በማዛመድ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ማደግ ይጠበቅባቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ቤተክርስቲያን ወደ ክርስቶስ ሙላት እንድትደርስ ከተሰጧት ስጦታዎች አንዱ ማስተማር ነው።

ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት፡-

- ክርስቶስን ማዕከል ያደረገ ሊሆን ይገባል።
- መጽሐፍ ቅዱሳዊ /It will be Sound Doctrine/ሊሆን ይገባል።
- የሰውን ህይወት የሚለውጥ እና ወደ ክርስቶስ የሚመልስ ሊሆን ይገባል።

- ለትምህርት፣ ለተግሳጽ፣ ልብን ለማቅናት፣ በጽድቅ ለቀለው ምክር የሚጠቅም ሊሆን ይገባል።
- ያልተሸቃቀጠ ሊሆን ይገባዋል(2ኛ ቆሮ 2፡17)።

## 4. ሕብረት

ሕብረት ማድረግ ማለት አብሮ መሆንን፣ ሀሳብ ለሃሳብ መቀባበልን፣ አብሮ መመካከርን፣ በሃዘን ይሁን በደስታ መደጋገፍን ያመለክታል።

አማኞች በክርስቶስ አካል ውስጥ ጠቃሚ መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል (ዕብ 10፡24-25)። ከዚህም በተጨማሪ መተናነጽ በመካከላቸው ይሆናል።

የማያምኑ ሰዎች እንኳ ሳይቀር የክርስቶስ ተከታዮች መሆናቸውን አውቀው ወደ ጌታ ዘወር እንዲሉ ይማርካቸዋል። ስለዚህ በምዕመናን መካከል የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖር ሕብረት የሚያደርጉበትን ሁኔታ በማመቻቸት የቤተክርስቲያን መሪዎች ኃላፊነታቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

ሕብረት ማድረግ ስንል ከአንድ አጥቢያ ባሻገር ያሉትንም ምዕመን ማሰብ ተገቢ ነው። ምክንያቱም ክርስቶስን የግል መድሃኒታቸው አድርገው የተቀበሉ ሁሉ የሁሉ አቀፏ ቤተክርስቲያን አካላት ናቸውና።

ከዚህ የተነሳ ሁላችንም አንድ አካል የአንድ አባት ልጆች ስለሆን ከእነርሱም ጋር ሕብረት ማድረግ አለብን። ይሁን እንጂ ሕብረት ስናደርግ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል። ምክንያቱም ሕብረት ማድረግ ያለብን ንፁሕ የሆነውን የክርስቶስን ትምህርት ከሚከተሉት ጋር እንጂ በትምህርታቸው የክርስቶስ ጠላቶች ከሆኑት ጋር መሆን የለበትም።

- **<u>የውጭ አገልግሎት</u>**

የውጭ አገልግሎት የምንለው ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ የማድረስ አገልግሎት ሲሆን ይህም የሁሉም ምዕመን ኃላፊነት ነው። ይሁን እንጂ ወንጌልን የማስፋፋት ቀዳሚ ኃላፊነት የአገልጋዮች ነው (ማቴ 28፡19-20)።

- አማኞች ወንጌልን በአግባቡ ለማስፋፋት የሚችሉት አስቀድመው፤
- የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት፤
- ለመጸለይና፤

www.holisticbiblecollege.org

- ወጥተውም ለመመስከር ፈቃደኞች ሆነው ሲገኙ እውን ይሆናል።

አማኞች የክርስቶስ ፍቅር ግድ የሚላቸው ከሆነ፣ ለወንጌል ስርጭት ከተነሳሱና ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ልባቸው ከቆረጠ በድፍረትና በጥበብ ማገልገል እንዲችሉ መንፈስ ቅዱስ ኃይልን ያስታጥቃቸዋል (ሐዋ 4፡31)።

www.holisticbiblecollege.org

# 1.5 የቤተክርስቲያን አስተዳደር

ቤተክርስቲያን ከጌታ ዘንድ የተሰጣትን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት እንድትችል የራሷ የሆነ አስተዳደር ሊኖራት ይገባል።

ይህም አስተዳደር አገልጋዮችና አጠቃላይ ምዕመናንን በማስተባበር ስራውን ማከናወን ይጠበቅበታል።

የቤተክርስቲያን መሪ በተለያዩ ስሞች ሊጠራ ይችላል። በቤተክርስቲያን የአስተዳደር ታሪክ ውስጥ በጣም ታዋቂ የሆኑ የአስተዳደር ዓይነቶች ከዚህ በታች እንመለከታለን።

**1. ጳጳሳዊ/ኤጲስቆጶሳዊ**

በአንድ ሊቀ ጳጳስ የሚመራ የአስተዳደር ዓይነት ሲሆን በዚሁ የአስተዳደር ዓይነት የሚመሩት የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ አንግሊካል ወዘተ ናቸው።

**2. ማህበረ ምዕመናዊ**

የምዕመኑን ሚና እና ውሳኔ የሚያጎላ የአስተዳደር ዓይነት ነው። በቤተክርስቲያን ያለን የማሕበረ ምዕመናን የሙብት፣ የሥልጣን፣ ነጻነትና እኩልነትን ለመደገፍ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ የተናገረው እንደማስረጃ ያቀርባል። *"እናንተ ግን፦ መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለ ሆነ እናንተም ሁላችሁ ወንድማማች ናችሁ።"* (ማቴ 23፡8)

በክርስቶስ ይሁን በጳውሎስ ትምህርት መሰረት የማሕበረ ምዕመናን ሙብትና ሥልጣን መሪዎችን መምረጥ ብቻ ሳይሆን ጥፋተኞችን ለመቅጣትም ሆነ ከጉባዔው ማስወገድም የማሕበሩ ሥልጣን ነው(ማቴ 18፡15-17፣ 1ኛ ቆሮ 1፡2/5)።

የሐዋሪያው የጳውሎስ መልዕክት ተቀባዮች ማንነት ለዚህ የማሕበረ ምዕመናዊ የአስተዳደር ዓይነት እንደ ማስረጃ ተደርጎ ይቆጠራል። ከዚህ የተነሳ ይህ የአመራር ዓይነት፦

- የእያንዳንዱን ምዕመናን ሚና ያጎላል፤
- መሪዎች በምዕመናን እጅ መሆን አለበት ይላሉ፤
- እረኛው ወይም መሪው የምዕመናን ጉዳይ አስፈጻሚ ተደርጎ ይታሰባል።

**3. ሽማግሌያዊ**



www.holisticbiblecollege.org

- ሙሉ ጊዜያቸው የሰጡና ከጉባኤው የተወከሉ በትርፍ ጊዜ የሚያገለግሉ መሪዎችን ያካትታል። የዚህ ዓይነት አስተዳደር የሚከተሉ ሜቶዲስት፣ ፕሪስባይተርያን እንዲሁም አንዳንድ ሉትራን ወዘተ ናቸው።
- በኢትዮጵያም ያለው የቤተክርስቲያን አመራርም የሚበዛው ሽማግሌያዊ ነው። ለምሳሌ፡- በአሁኑ ጊዜ በሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን እየተሰራበት ያለው አስተዳደር ዓይነት ሽማግሌያዊ ሲሆን እረኞች፣ ሙሉ ጊዜያቸውን ያልሰጡ ሽማግሌዎች፣ እንዲሁም ከአምስቱ የአገልግሎት ሥጦታዎችና ከዲያቆናት አንዳንድ ተወካዮች በመሆን ቤተክርስቲያኒቱን ይመራሉ። ይህም አመራር የመሪዎች ጉባዔ በመባል ይጠራል።

## 4. ጥምር አስተዳደር

- ጥምር አስተዳደር የሚባለው የመሪዎች ጉባዔ፣ የአስፈጻሚ አካል እና የዲሲፒሊን ራሳቸውን ችለው ሳይነጣጠሉ እየተመጋገሙ የሚመሩት ነው።
- ይህ አስተዳደር መሰረት የሚያደርገው *"እግዚአብሔር ፈራጃችን ነው፥ እግዚአብሔር ሕግን ሰጪያችን ነው፥ እግዚአብሔር ንጉሣችን ነው፤ እርሱ ያድነናል።"* (ኢሳ 33፡22)
- በጥቅሱ መሰረት አንዱ እግዚአብሔር ሕግ ሰጪ፣ ንጉስ እና ፈራጅ እንደሆነው ሁሉ አንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን በሶስት አደረጃጀት የሚከፍል ነው(ኢሳ 33፡22)።
- መሪዎች ጉባዔ የአጥቢያ እቅድና በጀት የሚቆጣጠር ሆኖ ከአባለት ይመረጣል።
- አስፈጻሚ አካል ደግሞ በአምስቱ አገልግሎት ሥጦታዎች የሚዋቀር ሲሆን በመሪ መጋቢው ይመራል።
- ዲሲፒሊን እንደ ዳኛ ጥፋት በሰሩ አባላት ላይ እርምጃ ይወስዳል።

www.holisticbiblecollege.org

# ማጠቃለያ

- ቤተክርስቲያን 500 እና 1000 ሰዎች በስምምነት የሚመሰርቷት የንግድ ማህበር ወይም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አይደለችም፡፡
- ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ የተጠራች የቅዱሳን ጉባኤ እንጂ ግዑዝ ህንጻ አይደለችም፡፡ ቤተክርስቲያን የሚሰገድለት ግዑዝ ህንጻ ሳትሆን በመንፈስና በእውነት ለእግዚአብሔር የሚሰግዱ ቅዱሳን ናቸው፡፡
- ቤተክርስቲያን የሚሰገድለት ግዑዝ ህንጻ ሳትሆን በመንፈስና በእውነት ለእግዚአብሔር የሚሰግዱ ቅዱሳን ናቸው፡፡
- የቤተክርስቲያን ስዕላዊ መገለጫዎች፡-
  - ✓ ራስና አካል፤
  - ✓ ሙሽራና ሙሽሪት፤
  - ✓ ግንድና ቅርንጫፍ፤
  - ✓ እረኛና መንጋ፤
  - ✓ ማዕዘን ራስ ድንጋይና ሕያዋን ድንጋዮች፤
- ቤተክርስቲያን ጌታ ኢየሱስ ሲከተሉ የነበሩ ምዕመናንም በተለያዩ ስሞች ይጠሩ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ ለመረዳት እንችላለን፡፡ ለምሳሌ፡-
  - ✓ አማኞች፤
  - ✓ ክርስቲያኖች፤
  - ✓ ወንድሞች፤
  - ✓ ቅዱሳን፤
  - ✓ የተመረጡ፡፡
- የቤተክርስቲያን ሥልጣን፡-
  - ✓ የዲያቢሎስ እና የሰራዊቱን ስራ ለማፍረስ፤
  - ✓ እንደ እግዚአብሔር ቃል የስነ-ስርዓት እርምጃ መውሰድ፤
  - ✓ ነፍሳትን ለማትረፍ እና ለመመለስ፡፡
- የቤተክርስቲያን አገልግሎት የውስጥ እና የውጭ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ የውስጥ አገልግሎት ማለት የክርስቶስን አካል ለማነጽ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለአማኞች

www.holisticbiblecollege.org

የሚደረገውን አገልግሎት የሚያመለክት ነው። የውጭ አገልግሎት የምንለው ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ የማድረስ አገልግሎት ሲሆን ይህም የሁሉም ምዕመን ኃላፊነት ነው።

- በቤተክርስቲያን የአስተዳደር ታሪክ ውስጥ በጣም ታዋቂ የሆኑ የአስተዳደር ዓይነቶች፡-
  - ✓ ጳጳሳዊ፣
  - ✓ ማህበረ ምዕመናዊ፣
  - ✓ ሽማግሌያዊ፣
  - ✓ ጥምር አስተዳደር።

www.holisticbiblecollege.org

# የክለሳ ጥያቄ አንድ

❖ **እውነት ወይም ውሸት**

1. "ቤተክርስቲያን" የሚለው ቃል ሕንጻን የሚያመለክት ነው።
2. ጥምር አስተዳደር የሚባለው የመሪዎች ጉባዔ፣ የአስፈጻሚ አካል እና የዲሲፕሊን ራሳቸውን ችለው ሳይነጣጠሉ እየተመጋገሙ የሚመሩት ነው።
3. ራስና አካል የክርስቶስ እና የቤተክርስቲያን ስዕላዊ መገለጫዎች ናቸው።
4. ጳጳሳዊ አስተዳደር የእያንዳንዱን ምዕመናን ሚና ያጎላል።
5. በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አስተምህሮና ቀኖና መሰረት ቤተክርስቲያን ለመትከል ጽላት/ታቦት ወሳኝ ነገር ነው።

❖ **ምርጫ**

1. በካቶሊክ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ መሰረት ቤተክርስቲያንን ለመትከል ምን ያስፈልጋል?
   **ሀ**) በሊቀ ጳጳሳቱ የተሾመ ካህን
   **ለ**) ጽላት/ታቦት ወሳኝ ነገር ነው
   **ሐ**) ዳግም የተወለዱ ክርስቲያኖች በቃሉ ዙሪያ መሰባሰብ አለባቸው
   **መ**) በሽማግሌዎች ጉባዔ የተሾመ አገልጋይ
2. ከሚከተሉት ውስጥ በዚህ ምዕራፍ ያልተዳሰሰው የትኛው ነው?
   **ሀ**) የቤተክርስቲያን ገጽታዎች
   **ለ**) የቤተክርስቲያን ሥልጣን
   **ሐ**) የቤተክርስቲያን አስተዳደር
   **መ**) የቤተክርስቲያን አገልግሎት
3. ከሚከተሉት የቤተክርስቲያን የውጭ አገልግሎት የሆነው የትኛው ነው?
   **ሀ**) አምልኮ
   **ለ**) ወንጌል ስርጭት
   **ሐ**) አስተምህሮ
   **መ**) ጸሎት
4. በኢትዮጵያ ብዙ ወንጌላዊያን አማኞች የሚከተሉት የአስተዳደር ስርዓቶች የትኛው ነው?
   **ሀ**) ጳጳዋዊ
   **ለ**) ማሕበረ ምዕመናን
   **ሐ**) ሽማግሌያዊ
   **መ**) ጥምር አስተዳደር

www.holisticbiblecollege.org

5. ከሚከተሉት ስለ ቤተክርስቲያን **ስህተት** ነው

**ሀ**) የእኔ ቤተክርስቲያን ማለት የምችለው ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው

**ለ**) በዚህ ዘመን የቤተክርስቲያን መስራቾች ሊኖሩ ይችላሉ

**ሐ**) የቤተክርስቲያን ባለቤት ኢየሱስ ነው

**መ**) የእኔ ቤተክርስቲያን ማለት ስህተት ነው

❖ **<u>አጭር መልስ</u>**

1. ቤተክርስቲያን ምንድናት?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

2. የቤተክርስቲያን አስተዳደር ዓይነቶችን ዘርዝር?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

3. የቤተክርስቲያን የውስጥ አገልግሎቶችን ዘርዝር?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

4. የቤተክርስቲያን ስዕላዊ መገለጫዎችን ዘርዝር?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

5. በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የተረዳኸውን ወይም አዲስ ያወከውን አጠር አድርገህ ግለጽ?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

www.holisticbiblecollege.org

# ምዕራፍ 2 የቤተ ክርስቲያን ገጽታዎች እና መለያዎች

| ማውጫ | |
|---|---|
| **ክፍል** | **መታወቅ ያለበት** |
| 2.1 ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን | • ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን እና አጥቢያ ቤተክርስቲያን ልዩነት አብራራ። |
| 2.2 የአጥቢያ ቤተክርስቲያን የጊዜ ቀመር | • አጥቢያ ቤተክርስቲያን በጊዜ ቀመር ያሳለፈችውን ምዕራፎችን አብራራ። |
| 2.3 የቤተክርስቲያን መለያዎች | • የቤተክርስቲያን መለያዎችን ጥቀስ። |

www.holisticbiblecollege.org

የአማኞች ስብስብ የሆነች ቤተክርስቲያን ሁለት ዓይነት ገጽታ አላት፤ እነዚህ ሁለት ገጽታዎች አብረን እንመልከት።

www.holisticbiblecollege.org

# 2.1 የቤተክርስቲያን ገጽታዎች

**1. ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን**

- *"በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ።"* (ኤፌ 4፡4) ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን አማኝ የተባሉትን ሁሉ የያዘች አንዲት ቅድስት ቤተክርስቲያን አንድ አካል ናት።

- ቤተክርስቲያን ከተወለደችበት ከጴንጤቆስጤ ዕለት አንስቶ እስከ መጨረሻው አማኝ ድረስ ያሉት በሙሉ በዚህች ቤተክርስቲያን ውስጥ ይጠቀለላሉ። ሁሉን አቃፏ ቤተክርስቲያን ሁሉን ዳግም የተወለዱ አማኞች ታቅፋለች (1ኛ ቆሮ. 15፡9፣ ገላ. 1፡13፣ ኤፌ. 5፡25-32)። አንድ ሰው የሁሉን አቀፏ ቤተክርስቲያን አካል ለመሆን መመዘኛው በክርስቶስ ማመን ብቻ ነው።

- ሁሉን አቀፏ ቤተክርስቲያን የማትታይ ቤተክርስቲያን ናት፣ መሪዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ ድርጅታዊ መዋቅር የላትም።

- ስማቸው በህይወት መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉት ብቻ አካል የሆኑባት ነው። ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን በጊዜና በቦታ አትወሰንም። በኢየሩሳሌም ያለች፣ በአንጾኪያ ያለች፣ በኢትዮጵያ ያለች ተብላ በቦታና በጊዜ ያልተወሰነች ዓለም አቀፋዊት ናት። በከተማ ስም፣ በገጠር ስም፣ በድርጅት ስም የማትጠራ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ናት።

- ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ ምድራዊ አገልግሎት ዘመን ጀምሮ የተጠሩትንና መንፈስ ቅዱስ ከወረደበት ከጴንጤቆስጤ ቀን ጀምሮ በክርስቶስ አምነው የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆኑትን ማለትም በክርስቶስ ሆነው ያንቀላፉትንና በሕይወት ያሉትን ሁሉ ያቀፈች ስትሆን እጅግ ብዙ ቁጥር ያላት ናት።

- ይህችን ቤተክርስቲያን አሁን ባለንበት ሁኔታ በአንድ ውስን ቦታ ተሰብስባ ማየት አይቻልም። ስለዚህ ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን ስንል አጠቃላይ የክርስቶስ አካል የሆነውን ህዝብ (ቆላ 1፡18-20፣ ኤፌ 1፡22-23፣ 1ኛ ጢሞ 3፡15) ማለታችን ነው።

## 2. አጥቢያ ቤተክርስቲያን



www.holisticbiblecollege.org

- አጥቢያ ቤተክርስቲያን የምትታይ ናት። ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን አንድ ስትሆን አጥቢያ ቤተክርስቲያን ግን በስፍራና በአካባቢ የተወሰነች ስለሆነች ብዙ ናት።
- ከአዲስ ኪዳን ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ብዙ አጥቢያ አብያተክርስቲያናት ነበሩ (ሮሜ 16፡5፣ 1ኛ ቆሮ 1፡2፣ ቆላ 4፡15) አሁንም በየስፍራው አሉ።
- አጥቢያ/Local ማለት አካባቢ ወይም ቀበሌ እንደማለት ነው። እነዚህ ምዕመናን በህንጻ ውስጥ አመለኩ ወይም በቤት አጥቢያ፤ አጥቢያ ተብለው ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ፡- ኢየሩሳሌም፣ ፍልጵስዩስ፣ ተሰሎንቄ፣ ኤፌሶን፣ በሮም በአቂላና ጵርስቅላ ቤት ያለችው ቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው።
- የአንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አምኖ ንስሃ ከመግባት ባሻገር የውሃ ጥምቀት ስርዓት መውሰድና የቤተክርስቲያኒቱን የእምነት አቋምን መቀበልን ይጠይቃል (ሐዋ 2፡41)።
- አጥቢያ ቤተክርስቲያን በአንድ መልክዓ ምድራዊ አካባቢ የሚገኙ ክርስቲያኖች አንድ እምነት ስላላቸው በአንድነት ጌታን ለማምለክ፣ ቃሉን ለመማር፣ እርስ በርስም ለመተናነጽ ወንጌልን ለማዳረስና የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ሁሉ ለመፈጸም በአካባቢያቸው የተደራጁ ምዕመናን ስብስብ ናት።
- *"ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፥ በከተማ ፍርሃት፥ በምድረ በዳ ፍርሃት፥ በባሕር ፍርሃት፥ <u>በውሸተኞች ወንድሞች</u> በኩል ፍርሃት ነበረብኝ።"* (2ኛ ቆሮ 11፡26) በ2ኛ ቆሮንቶስ መልዕክት መሰረት በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ያልዳኑ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በገላቲያ መልዕክቱም በገላቲያ አብያተክርስቲያናት የሕግ ባሪያዎች ሊያደርጉ መጽደቅ ኢየሱስ ላይ ሕግ ሲጨመር ነው ብለው የሚያስተምሩ ሀሰተኞች እንደነበሩ መረዳት እንችላለን። በ*"ባሪያዎች ሊያደርጉን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን አርነታችንን ይሰልሉ ዘንድ ሾልከው በስውር ስለ ገቡ ስለ ሐሰተኞች ወንድሞች ነበረ።"* (ገላ 2፡4)
- አጥቢያ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ ተቋም ብትሆንም በምድር ድርጅታዊ መዋቅር ሊኖራት ይችላል። *"<u>የቀረውን እንድታደራጅ</u> በየከተማውም፥ እኔ አንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ።"* (ቲቶ 1፡5) ከዚህ ክፍል አጥቢያ ቤተክርስቲያን ተቋማዊ አደረጃጀት ሊኖራት እንደሚችል መረዳት ይቻላል። አጥቢያ ቤተክርስቲያን ሕያው አካል(Organism) እና ተቋማዊ(Organizational) ናት።



www.holisticbiblecollege.org

- በምድር ያለችውን የቤተክርስቲያን ልዩ ተቋም የሚያደርጋት ዓላማዋ መንፈሳዊ በመሆኑ እና የበላይ ጠባቂዋ ኢየሱስ ክርስቶስ በመሆኗ ነው።
- አንዳንዶች ድርጅታዊ መዋቅር/Organizational Structure ለመንፈስ ቅዱስ አሰራር አይመችም ብለው ይህን አይቀበሉም። ነገር ግን ድርጅታዊ መዋቅር የመንፈስ ቅዱስን አሰራር ለመጨፍለቅ አይደለም። እግዚአብሔር የስርዓት አምላክ በመሆኑ ስርዓት ያላት እንድትሆን በምድር ወንጌልን ለማስፋፋት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ያለው አደረጃጀት ቢኖራት የተሻለ ነው(1ኛ ቆሮ 14፡33)።
- አጥቢያ ቤተክርስቲያን በመልክዓ ምድር ልትጠራ ትችላለች። ለምሳሌ፡- ብንጠቅስ
  - ✓ በኢየሩሳሌም ያለች ቤተክርስቲያን- ሐዋ 8፡1፤ 11፡22
  - ✓ በአንፆክያ ያለችው ቤተክርስቲያን- ሐዋ 13፡1
  - ✓ በኤፌሶን ያለችው ቤተክርስቲያን- ሐዋ 20፡17
  - ✓ በገላትያ ያሉት አብያተክርስቲያናት- ገላ 1፡2
  - ✓ በእስያ ያሉት አብያተክርስቲያናት- ራዕ 1፡4 ተጠቃሽ ናቸው።
- አጥቢያ ቤተክርስቲያን ወንጌልን ለማዳረስ የቤተክርስቲያን ስርዓቶችን ማለትም የጌታ እራትና የውኃ ጥምቀትን ለመፈጸም፣ ህብረት ለማድረግና እርስ በርስ ለመተናነጽ ዓይነተኛዋና ብቸኛዋ መስክ ናት። አንድ ሰው ድነትን ሲቀበል ፍጹም ሆነ ማለት ስላይደለ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አባላት ፍጹማን አይደሉም። እንዲያውም ምናልባት የዳኑ የሚመስሉ ግን ያልዳኑ ሰዎች ወደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነት በስህተት ሊገቡ ይችሉ ይሆናል።
- ዛሬም በዘመናችንና በአካባቢያችን የሚገኙ ብዙ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ልንጠራ እንችላለን። የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን፤ የወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን፣ የሙሉ ወንጌል ቤተክርስቲያን፣ የመሰረተ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ የሕይወት ብርሃን ቤተክርስቲያን፣ የአማኑኤል ሕብረት ቤተክርስቲያን፣ የክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ ወዘተ.... እንደምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው።

www.holisticbiblecollege.org

# 2.2 የአጥቢያ ቤተክርስቲያን የጊዜ ቀመር

አጥቢያ ቤተክርስቲያን በጊዜ ቀመር ልትታይ ትችላለች። የሚከተሉት ከጅማሬዋ እስካሁን ድረስ ያለችውን አጥቢያ ቤተክርስቲያን የጊዜ ቀመር ነው።

1. **የሐዋርያት ቤተክርስቲያን፡-** በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ እና በመንፈስ ቅዱስ መፍሰስ ከክርስቶስ እርገት በኋላ የተመሰረተችውን ቤተክርስቲያን ያመለክታል።
2. **የጥንቷ ቤተክርስቲያን፡-** ከሐዋርያት ማረፍ በኋላ የቤተክርስቲያን አባቶች ተብለው በሚጠሩት ትመራ የነበረችውን ቤተክርስቲያን ያመለክታል።
3. **የመካከለኛ ዘመን ቤተክርስቲያን፡-** በካቶሊክ ቤተክርስቲያን መሪነት ላይ የወደቀ የቤተክርስቲያን አስተዳደር የሚታይበት በርካታ አስተዳደራዊ እና አስተምህሮአዊ ግድፈት የታበት እና ቤተክርስቲያንን ወደ ጨለማ ያስገባ የውድቀት ዘመንን ያሳያል።
4. **የተሐድሶ ዘመን ቤተክርስቲያን፡-** ይህ ዘመን እንደ እነ ማርቲን ሉተር፣ ዮሐንስ ካልቪን፣ ዚውንግሊን፣ ኤራስመስን የመሰሉ የተሐድሶ አራማጆች የተነሱበት ዘመን ነው። ለክርስትና እውነት ዳግም በኃይል መነሳት ትልቅ እምርታ ያሳየ ዘመን ነው።
5. **የዘመናችን ቤተክርስቲያን፡-** ይህ አሁን ያለንበትን ዘመን የሚያመለክት ነው።

www.holisticbiblecollege.org

# 2.3 የቤተክርስቲያን መለያዎች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ምን መምሰል እንዳለባት በአጭር ቃል እንዲህ ነው ተብሎ ባይገለጽም ምን መሆን እና ማድረግ እንዳለባት ለማወቅ የሚረዱ መለያዎችን በስፋት እናገኛለን።

ጊርትሰን (Glertson 1992, ገጽ 8-9) የተባለ ሰው የቤተክርስቲያንን መለያዎች ሲገልጽ በአራት ከፍሎታል ይህም ቅድስት፣ አንዲት፣ ካቶሊካዊትና ሐዋርያዊት ናት በማለት ነው። እነዚህ አራቱ መለያዎች እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ምን መምሰል እንዳለት እንደሚገባ የሚገልጹ ስለሆነ ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታቸዋለን።

## 1. ቤተክርስቲያን ቅድስት ናት

ቅድስና ማለት መለየት ማለት ሲሆን በዚህ ክፍል የምንመለከተው ቅድስና አማኞች በዕለታዊ ኑሮአቸው ሊታይ የሚገባውን የሕይወት ንፅሕና የሚያመለክት ነው (1ኛ ጴጥ 1፡15-16)።

ቤተክርስቲያን ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ የሚያደርጋት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሔር የተመረጠችና ለርስቱ የተለየች ወገን እንድትሆን ቀድሷታል(ዮሐ 17፡19፣ 1ኛ ቆሮ 6፡11)። ይህም ቅድስና የአማኞች የእለት ተእለት ኑሮ የሚያሳይ ሳይሆን የእግዚአብሔር ወገን ለመሆን በንስሃ ከክርስቶስ ጋር ህብረት ባደረጉበት ጊዜ በቅጽበት የሚሆን ቅድስና ነው (1ኛ ቆሮ 6:11፣ 1ኛ ጴጥ 2:9)። ይሁን እንጂ በእለታዊ ኑሮም በቅድስና መኖር እንዳለባት የእግዚአብሔር ቃል አበክሮ ይናገራል (2ኛ ተሰ 4:27)። ምክንያቱም ቅድስናን የማታውቅ ቤተክርስቲያን ክርስቶስንም ስለማታውቅ ነው(ራዕ 2:3)።

ቤተክርስቲያንን ጌታ እንደቀደሳት ራሷንን ከዓለም ጋር ሳታመሳስልና ሳታመቻምች በቅድስና መኖር ይጠበቅባታል(2ኛ ቆሮ 6፡14-18)።

## 2. አንዲት ናት

አንድነት ህብረትን የሚያሳይ ሲሆን አማኞች በክርስቶስ ኢየሱስ በመንፈስ እና በእምነት አንድ መሆናቸውና አንድነታቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው የሚያመለክት ነው።

ጌታ ኢየሱስ እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ ብሎ ስለ አማኞች አንድነት እንደጸለየና(ዮሐ 17፡22) መንፈስ ቅዱስም አንድነቱን እንደመሰረተው የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳል(ኤፌ 4፡3)።

ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 16፡ 18 ላይ የተናገረው ስለ አንዲት ቤተክርስቲያን ሲሆን እኛም በአንዲት ቤተክርስቲያን እናምናለን። የቤተክርስቲያን አንድነት የመንፈስ ቅዱስ ስራ ሲሆን ይህም ወደ አንድ አካል (የክርስቶስ አካል) በመሰነቅ (1ኛ ቆሮ 12፡13) ይጀምራል። ምንም እንኳ በቤተክርስቲያን ውስጥ ልክ እንደ አካል ብልቶች ምዕመናን ልዩ ልዩ ስጦታ ቢኖራቸውም ቤተክርስቲያን አንድ አካል ናት። ይህንንም አንድነት ጠብቆ መኖር የሚቻለውም አንድነትን በሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ሲሆን አማኞች በትህትና ሁሉ፣ በየዋህነት፣ በትእግስትም ጭምር ሆነው ሲተጉ ነው። ስለዚህ አማኞች የአንድ አባት ልጆችና በክርስቶስ በኩል ለአንድነትም እንደተጠሩ በመገንዘብ ሁልጊዜ አንድነታቸውን ለመጠበቅ መትጋት ይኖርባቸዋል።

## 3. ካቶሊካዊት ናት

ካቶሊካዊት ስንል ፍጹም የሆነችው ወይም ዓለም አቀፍ የሆነችው ለማለት ሲሆን ቤተክርስቲያን እውነተኛውን እምነት አጽንታ በመያዝ የሐሰት ትምህርትን ስትቃወም የተጠቀችበት ስም ነበር። የሮማን ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ግን ይህንን ስም ለራሷ በመውሰድ የተጠቀመችበት ሲሆን የተሐድሶ አራማጆች (Reformers) ደግሞ ይህንን ስም ለእውነተኛ ወይም ትክክለኛ ለሆነው እምነት እንጂ በአካባቢ የተወሰነችው ቤተክርስቲያን ስለማይጠቀሙበት የሮማን ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በማስጠንቀቅ ተቃወሙ። ይሁን እንጂ የሮማን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን አልሰማቻቸውም።

www.holisticbiblecollege.org

እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ለዘር፣ ለቀለም፣ ለማህበራዊ ደረጃ፣ ለእውቀት ወዘተ የልዩነት ቦታ ሳትሰጥ በእምነትና በመንፈስ አንድ ሆና የምትኖር ናት።

## 4. ሐዋርያዊት ናት (Apostolic)

አንዲት ቤተክርስቲያን የሐዋርያት ትምህርትና እምነት ከተቀበለች ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ትባላለች።

ይህም የሚያሳየን ቤተክርስቲያን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ መመስረትና በምታድርገው አጠቃላይ እንቅስቃሴና የእድገት አቅጣጫም ራሷን የምትመዝንበት መመርያ ወይም መለኪያ አድርጋ መውሰድን ይጠይቃል።

# ማጠቃለያ

- ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያንን ማለት ክርስቶስን አምነው የተቀበሉት ከዚህ በፊት ኖረው የሞቱት፤ አሁን በህይወት ያሉትና ወደፊትም የሚኖሩት አማኞች በሙሉ የሚጠቃለሉበት ስብስብ ነው።
- አጥቢያ ማለት አካባቢ፣ ቀበሌ ማለት ነው። እነዚህ ምዕመናን በህንጻ ውስጥ አመለኩ ወይም በቤት አጥቢያ፣ አጥቢያ ተብለው ተጠቅሰዋል። ለምሳሌ፡- ኢየሩሳሌም፣ ፍልጵስዩስ፣ ተሰሎንቄ፣ ኤፌሶን፣ በሮም በአቂላና ጵርስቅላ ቤት ያለችው ቤተ ክርስቲያን ምሳሌዎች ናቸው።
- የእውነተኛዋ ቤተክርስቲያን መለያዎች፡-
  - ✓ ቅድስት፣
  - ✓ አንዲት፣
  - ✓ ካቶሊካዊት፣
  - ✓ ሐዋሪያዊት።

www.holisticbiblecollege.org

# የክለሳ ጥያቄ ሁለት

❖ **እውነት ወይም ውሸት**

1. ቤተክርስቲያን ከተወለደችበት ከጴንጤቆስጤ ዕለት አንስቶ እስከ መጨረሻው አማኝ ድረስ ያሉት በሙሉ በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ይጠቀለላሉ።
2. አጥቢያ ቤተክርስቲያን የምትታይ ናት።
3. በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ አማኝ የተቀደሰ ሰው ነው።
4. ቤተክርስቲያን ካቶሊካዊት አይደለችም።
5. እውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ለዘር፣ ለቀለም፣ ለማህበራዊ ደረጃ፣ ለእውቀት ወዘተ የልዩነት ቦታ ሳትሰጥ በእምነት እና በመንፈስ አንድ ሆና የምትኖር ናት።

❖ **ምርጫ**

1. ከሚከተሉት ውስጥ በዚህ ምዕራፍ **ያልተዳሰሰው** የትኛው ነው?
   **ሀ**) የአጥቢያ ቤተክርስቲያን የጊዜ ቀመር
   **ለ**) የቤተክርስቲያን አስተዳደር
   **ሐ**) ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት
2. ከሚከተሉት ውስጥ የቤተክርስቲያን መለያ **ያልሆነው** የትኛው ነው?
   **ሀ**) ካቶሊካዊት
   **ለ**) ሐዋሪያዊት
   **ሐ**) አንዲት
   **መ**) አጥቢያ ቤተክርስቲያን
3. ከሚከተሉት የቤተክርስቲያን ገጽታ **ያልሆነው** የትኛው ነው?
   **ሀ**) ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን
   **ለ**) አጥቢያ ቤተክርስቲያን
   **ሐ**) ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን
   **መ**) ሁሉም መልስ ነው
4. ከሚከተሉት ውስጥ **ውሸት** የሆነው የትኛው ነው?
   **ሀ**) ኢየሱስ ክርስቶስ የአማኞች ቅድስና ነው
   **ለ**) በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ቅዱሳን ናቸው
   **ሐ**) አማኖች ጌታ እንደቀደሳቸው መቀደስ አለባቸው
   **መ**) መልስ የለም

www.holisticbiblecollege.org

**5.** ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ ያለአግባብ በአገልግሎት ስለ ዋለ የተሐድሶ አራማጆች የተቃወሙት የትኛውን ነው?

**ሀ**) ካቶሊካዊት

**ለ**) ሐዋሪያዊት

**ሐ**) አንዲት

**መ**) ቅድስት

❖ **አጭር መልስ**

1. የቤተክርስቲያን ሁለት የመገለጫ ገጽታዎች ምን ምን ናቸው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

2. ሁሉ አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

3. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

4. አንድ አማኝ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሆን ለምን ያስፈልገዋል?

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

5. በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የተረዳኸውን ወይም አዲስ ያወከውን አጠር አድርገህ ግለጽ?

---------------------------------------------------------------------------------------------------

www.holisticbiblecollege.org

www.holisticbiblecollege.org

# ምዕራፍ 3 የቤተክርስቲያን ስርዓቶች

**ማውጫ**

| ክፍል | መታወቅ ያለበት |
|---|---|
| 2.1 የውኃ ጥምቀት | • ስድስት ዓይነት ጥምቀቶችን ጥቀስ።<br>• መጠመቅ ያለባቸው እነማን ናቸው።<br>• በውኃ ጥምቀት መንግሥተ ሰማይ መግባት ይቻላል።<br>• በማን ስም እንጠመቅ። |
| 2.2 የጌታ እራት | • የጌታ እራት ዓላማ ምንድነው።<br>• የጌታ እራት ለመውሰድ የሚችል ሰው ማነው።<br>• የጌታ እራት ከምን ይዘጋጅ።<br>• ስርዓቱን በመስጠት ማን ያገልግል።<br>• የጌታ እራት ከመካፈል የሚያግዱ ነገሮች ምንድናቸው።<br>• የጌታ እራት በስንት ጊዜ እንካፈል። |
| 2.3 ልዩ ልዩ ስርዓቶችን ማስፈጸም | • ተጨማሪ የቤተክርስቲያን ስርዓቶችን ዘርዝር። |

www.holisticbibleco

ጌታ ኢየሱስ በክብር ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት ሁለት ሕያው የሆኑ ስርዓቶችን ለቤተክርስቲያን ሰጥቷል። እነርሱም የጌታ እራት እና የውሃ ጥምቀት ናቸው። ሁለቱም ስርዓቶችና በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚፈጸሙ ሌሎች ስርዓቶች ጨምረን ከዚህ በታች በዝርዝር ለመመልከት እንሞክራለን።

## 3.1 የውሃ ጥምቀት

*"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"* (ማቴ 28፡19-20)

ስለ ውሃ ጥምቀት ከመመልከታችን በፊት በአጠቃላይ ጥምቀት የሚለው ቃል ትርጉምና የጥምቀት ዓይነቶችን ከዚህ በታች እንመለከታለን። ጥምቀት የሚለው ቃል "ባፕቲዞ" ከሚል የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጓሜው መስጠም ወይም መሸፈን ማለት ነው። ሌላው ትርጓሜው ደግሞ በአንድ ነገር ተጽዕኖ ስር መሆን ማለት ነው።

**በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ የተገለጹ ስድስት ዓይነት ጥምቀቶች አሉ። እነርሱም**

### 1. የአይሁድ ጥምቀት

*"ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ።"* (1ኛ ቆሮ 10፡2)

አይሁዳዊያን የረከሰው እንዲነጻ፣ በድን የነካው፣ ከለምጹ የነጻው ብቁ እንዲሆን የማጥመቅ ልማድ ነበራቸው። ይህ የአይሁዳዊን ጥምቀት ውጫዊ አካልን ወይም ሥጋን የሚያነጻ ነው። ለኃጢአት ስርየት ለመቀደስ አይሆንም ነበረ። ስለዚህ በውስጡ ዕረፍት እና ኃይል አልነበረውም። በዘመናችንም የኃጢአት ይቅርታ፣ የቅድስና አቅም ሲናፈቅ ኖሯል።

### 2. ዮሐንስ ጥምቀት

*"ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር።"* (ማቴ 3፡6)

የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ከክርስቲያን ጥምቀት የቀደመ የብሉይ ኪዳን ጥምቀት ነው። የዮሐንስ ጥምቀት የንስሐ ጥምቀት ነው። ሰዎች ኃጢአታቸውን ከተናዘዙ በኋላ ያጠምቃቸው ነበር።

የዮሐንስ ጥምቀት ዋና ዓላማ ስለ መሲሁ ማለት ስለክርስቶስ በመስበክ ሰዎች ንስሃ ገብተው ተዘጋጅተው እንዲጠብቁትና ሲመጣም እንዲቀበሉት ለማድረግ ነበር (ማቴ 3፡11-12፣ ማር 1፡1-

8፣ ሉቃ 3፡3-6)። ይህ ጥምቀት በመጥምቁ ዩሐንስ የንስሀ ስብከት ክርስቶስን እንዲያምኑ ለንስሀ ያዘጋጅ የነበር ጥምቀት ነው።

ጌታም ራሱ በ30 ዓመቱ በዮርዳኖስ ውሃ በዮሐንስ እጅ ተጠምቋል። ጌታችን የተጠመቀው ሌሎቹ እንደሚያደርጉት ኃጢአቱን ለመናዘዝ ወይም ለመዘጋጀት ሳይሆን ጽድቅ ሁሉ ክርስቲያን በውኀ የሚጠመቀው ለደኅንነት አይለም።

### 3. የመከራ ጥምቀት

*"ኢየሱስ ግን መልሶ፦ የምትለምኑትን ኢታውቁም። እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አለ።"* (ማቴ 20፡22)

ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን የተጠመቀው የመከራ ጥምቀት ነው። ይህም ከዛሬ ሁለት ሺ ዓመት በፊት ተከናውኗል። እኛን ወክሎ የተቀበለው የመከራ ጽዋ ጥምቀት ነው(ማቴ 26፡39)።

www.holisticbiblecollege.org

### 4. ወደ ክርስቶስ መጠመቅ(የአካል ጥምቀት)

*"አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል"* (1ኛ ቆሮ 12፡13)

*"በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት።"* (ኤፌ 4፡4-5)

አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ወዲያውኑ የእግዚአብሔር ልጅነቱ እንዲጸና በመንፈስ ቅዱስ ወደ ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን አካል የሚጨመርበት ጥምቀት ነው።

### 5. የውሃ ጥምቀት

*"ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን ኢታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን።"* (ሮሜ 6፡3-5)

በዚህ ክፍል የምንማረው ክርስቲያን የሚፈፀመውን የውሃ ጥምቀት ነው። የውሃ ጥምቀት ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛቸው አድርገው ከተቀበሉ በኋላ የሚወስዱት ጥምቀት ነው።

የውኃ ጥምቀት ምሳሌያዊ የውህደት ወይም የአንድነት መግለጫ ድርጊት ነው፤ የሚያመለክተውም አማኝ ከክርስቶስ ጋር ሕብረት ማድረጉን ነው (ቆላ. 2፡11-13)። አንድ አማኝ ክርስቶስን ባመነ ጊዜ የተለወጠውን የውስጥ ለውጥ በውጪያዊና በሚታይ መንገድ በአደባባይ በውኃ ጥምቀት ይመሰክራል።

## 6. የእሳት ጥምቀት

*"እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ <u>በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል፤</u> መንሹም በእጁ ነው፥ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፥ <u>ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፥ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።"</u>* (ማቴ 3፡11-12)

ይህን ጥምቀት የሚያጠምቀው ራሱ ክርስቶስ ነው። የእሳት ጥምቀት ፍርድ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ያልተቀበሉት የሚጠመቁት ጥምቀት ነው።

### አማኞች የውሃ ጥምቀት የሚወስዱበት ምክንያት

- የጌታ ትዕዛዝ ስለሆነ(ማቴ 28፡19-20፣ ማር 16፡16)
- ሐዋርያትና ቅዱሳን ሁሉ ይህንን ሥርዓት ስለፈጸሙ (ሐዋ 8፡12፣ 10፡47-48፣ 26፡40)
- የክርስቲያን ጥምቀት አማኙ በክርስቶስ ማመኑንና መለወጡን በይፋ የሚመሰክርበት ስርዓት ስለሆነ (ገላ 3፡26)።
- አማኞች ከጌታ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ጋር መተባበራቸውን በእምነት የሚገልፁበት መንገድ ስለሆነ ነው(ሮሜ 6፡4-11)።



  እምነታቸውን ለዓለም፣ ለሰይጣን ሃሳብና ለኃጢአት ሞቻለሁ በአዲስ ሕይወት ለመመላለስ ደግሞ ተነስቻለሁ በማለት ከጌታ ጋር ሕብረታቸውን በመግለፅ የሚመሰክሩበት ስርዓት ነው። መጠመቅ ከጌታ ኢየሱስ ሞትና ትንሳኤ ጋር መተባበራችንን የምንገልጽበትና በህዝብ ፊት ስለ ጌታ የምንመሰክበርበት አንዱ መንገድ መሆኑን መዘንጋት የለብንም። አንድ ክርስቲያን የሚጠመቅበት ምክንያት የጌታ ትዕዛዝ ስለሆነ እርሱን ለመታዘዝ እና የውስጡን ለውጥ በውጪያዊ መግለጫ

www.holisticbiblecollege.org

ለመግለጥ ማለትም ለኃጢአት ሞቶ ለጽድቅ መነሳቱን ለማወጅ በዚህም ከቤተ ክርስቲያን ጋር አንድ መሆኑን ለማሳወቅ ነው።

አለመጠመቅ አለመታዘዝ ነውና። መታዘዝ ደግሞ እግዚአብሔርን ማክበር ስለሆነ ስርዓቱን በኢጥቢያ ቤተክርስቲያን መሪዎች አስፈጻሚነት መፈፀም ይኖርብናል።

**መጠመቅ ያለባቸው እነማን ናቸው?**

ሐዋ 2፡14-47 ያንብቡ!

አንድ ሰው ከመጠመቁ በፊት ማሟላት የሚገባቸው ሶስት ነገሮች፡-

- የወንጌል ትምህርት፣
- እምነት፣
- ንስሃ፣

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትዕዛዝ ያመኑ ሁሉና ያመኑ ብቻ መጠመቅ አለባቸው (ሐዋ. 2፡41፣ 8፡ 12፣ 36-38፣ 16፡14-15፣ 30-33፣ 18፡8፣ 19፡4-5)። ማንም ክርስቲያን የወንጌሉን የምስራች ቃል ከሰማ በኋላ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን እንደ ግል መድኃኒቱ ከተቀበለ በኋላ የውስጡን ለውጥ በጥምቀት መመስከር እንደሚገባው ካወቀ መጠመቅ ይችላል።

አንዳንድ ወንጌላዊያን አብያተክርስቲያናት የሕጻናት ጥምቀትን ይቀበላሉ። ይህ እንደ ኑፋቄ ትምህርት የሚወገዝ ባይሆንም መዳን በጥምቀት ነው ወይም ኢየሱስ ሲደመር ጥምቀት የሚል ከታከለበት ውጉዝ ትምህርት ነው።

**በውሃ ጥምቀት መንግሥተ ሰማይ መግባት ይቻላል?**

*"ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም። ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል፥ የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፥ ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ፥ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው።"* (1ኛ ጴጥ 3፡20-21)

የውሃ ጥምቀትን በተመለከተ ልብ ልንለው የሚገባን ነገር ቢኖር ምንም እንኳ የውሃ ጥምቀት ባያድንም የእግዚአብሔር ቃል የውሃ ጥምቀት መውሰድ እንዳለብን ስለሚያዘን መታዘዝ አለብን።

የዘላለም ህይወት በጥምቀት አይገኝም። ለዘላለም ህይወት ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ ለምን ተጠመቀ? ከኢየሱስ ቀኝ በኩል የተሰቀለው የዘላለምን ሕይወት ያገኘው ስለተጠቀ አይደለም። ስለዳንን እንጠመቃለን እንጂ ለመዳን አንጠመቅም። የውሃ ጥምቀት ደህንነት አያመጣም ምክንያቱም ደህንነት የተመሰረተው የእግዚአብሔር ፀጋ ላይ ነው። ይህ ጸጋ ደግሞ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ ማመንን ይጠይቃል።

ደህንነት የሚገኘው ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን አውቆ ስለኃጢአቱ የሞተውን ጌታ ኢየሱስን በንስሃ በመቀበል ብቻ ነው(ሮሜ 6፡23፣ 1ኛ ጢሞ 1፡15)። ስለዚህ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ በኩል ካልታረቀ በስተቀር የውሃ ጥምቀት በመውሰድ ሊድን አይችልም።

## በማን ስም እንጠመቅ?

ማንም ክርስቲያን የወንጌሉን የምስራች ቃል ከሰማ በኋላ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን እንደ ግል መድኃኒቱ ከተቀበለ በኋላ የውስጡን ለውጥ በጥምቀት መመስከር እንደሚገባው ካወቀ መጠመቅ ይችላል።

አንድ ክርስቲያን መጠመቅ ያለበት እንደ ጌታ ትዕዛዝ በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው። በሐዋርያት ሥራ ውስጥ በኢየሱስ ስም የመጠመቅ ነገር ተዘግቧል። ይህ ማለት የመጀመሪያው አሳብ መሻሩ ሳይሆን በወቅቱ ኢየሱስን እንደ መሲህ ለመቀበል የነበረውን ችግር ለማስወገድ አትኩረትን በኢየሱስ ላይ ለማድረግ ነው እንጂ ትምህርተ ሥላሴን ውድቅ የማድረጋቸው እርምጃ ወይም *"በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም"* የተባሉትን መሻራቸው ወይም በዚያ ስም ያለማጥመቃቸው አልነበረም። ሰው አንድ ጊዜ ካመነ በኋላ መጠመቅ አለበት።

# 3.2 የጌታ እራት

ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ከጥምቀት ቀጥለው ይፈጽሙት ዘንድ በቋሚነት ከሰጣቸው ስርዓቶች ሁለተኛው የጌታ ዕራት ነው (ማር 14፡22-26፣ ሉቃ 22፡17-20፣ 1ኛ ቆሮ 11፡23-34)። "ቁርባን" የሚለው የግዕዝ ቃል "መቅረብ" ከሚለው የዕብራይስጥ ስርወ-ቃል የወጣ ነው።

በብሉይ ኪዳን በዘጸአት 12 የፋሲካ በግ ታሪክ እናገኛለን። ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ. 5፡ 7-8 ይህን ሲያወሳና ከዚህ ስርዓት ጋር ሲያያይዘው እናያለን። ይህን ስርዓት የደነገገው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ነው። የፋሲካ በዓል ዋና ዓላማ እስራኤል ከግብጽ የመውጣታቸው መታሰቢያ ነው። ከጌታ ጋር እራቱን ሲበሉ ጌታ እንደተናገራቸው እንጀራው የስጋው፤ ጽዋው ደግሞ የደሙ ምሳሌዎች ናቸው። እነዚህ ነገሮች መታሰቢያ ብቻ ናቸውና የሚሰሩት ከህብስትና ከወይን ነው። ስያሜዎች፡-

- ✓ የጌታ እራት (1ኛ ቆሮ 11፡20)
- ✓ የጌታ ማዕድ(1ኛ ቆሮ 10፡21)
- ✓ እንጀራን መቁረስ (ሐዋ 2፡42)

**1ኛ ቆሮ 11፡23-34 ያንብቡ!**

የጌታ እራት የኃጢአት ስርየት ማግኛ ወይም የደህንነት መንገድ አይደለም። ነገር ግን በጌታ ሞት ምክንያት መዳናችንን የምናስታውስበት፣ የጌታን መምጣት ተስፋ የምናስብበትና የምንናገርበት፤ አንድ እንጀራ በመቁረሳችንና አንድ ጽዋ በመጠጣታችን በአንድነታችን የምንደሰትበት ጊዜ ነው።

የሰጠውም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን እራት በሚበሉበት ጊዜ ነው። የፋሲካ በዓል ዋና ዓላማ እስራኤል ከግብጽ የመውጣታቸው መታሰቢያ ነው። የጌታ እራት ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ሲል ስጋውን መቁረሱንና ደሙን ማፍሰሱን ደቀ መዛሙርቱን እንዲያስታውሱ የሰጣቸው ስርዓት ነው። በኢየሩሳሌም በነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ይህን ስርዓት በኅብረት ያደርጉ ነበር (ሐዋ. 2፡42)። ከጌታ ጋር እራቱን ሲበሉ ጌታ እንደተናገራቸው እንጀራው የስጋው፤ ጽዋው ደግሞ የደሙ ምሳሌዎች ናቸው። እነዚህ ነገሮች መታሰቢያ ብቻ ናቸውና የሚሰሩት ከህብስትና ከወይን ነው። የጌታ እራት ወይም ቅዱስ ቁርባን በሚወሰድበት መታሰብ የሚገባቸው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው ጌታ ስለሰው ልጆች ሲል በመስቀል ላይ መሞቱን (1ኛ ቆሮ. 11፡26) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ወደፊት ሊሆን ያለውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓትን ነው (1ኛ ቆሮ. 11፡2)።

www.holisticbiblecollege.org

ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ስርዓት የሚሳተፉት ሊመለከቱ የሚገባቸው ሌላ አቅጣጫም አለ፤ ይህም ወደ ራሳቸው (ወደ ውስጥ ህይወት) ነው (1ኛ ቆሮ. 11፡28)። ይህም ማለት የጌታ እራት መታሰቢያ ከመካፈላቸው በፊት አማኞች ራሳቸውን መመርመር ማለትም ከእግዚአብሔርም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ መሆኑን መመርመር ይገባቸዋል ማለት ነው። በሕይወታቸው ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ቢኖር መታሰቢያውን ከመውሰድ መቆጠብና ችግሮቻቸውን ቃሉ በሚለው መንገድ መፍታት ይኖርባቸዋል።

አማኞች ሁሉ የጌታን እራት የመካፈል መብት ቢኖራቸውም የሚካፈሉት ሁሉ ግን የተገባቸውና የገባቸው ሊሆኑ ያስፈልጋል (1ኛ ቆሮ. 11፡27-32)። የተገባቸው ማለት ከላይ እንደተመለከትነው የዳኑና (ደህንነትን ያገኙ) በተጨማሪም በዚያ ጊዜ ከጌታም ሆነ ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ የሆነ ማለት ነው። የገባቸው ማለት ደግሞ የጌታ እራት ምንነቱን የተረዱ ማለት ነው። ያለአግባብ የጌታን እራት መካፈል ድካምን፣ ህመምን፣ ስጋዊ ሞትን ፍርድንና ኩነኔንም ያስከትላል።

ክርስቲያኖች የጌታን እራት በሚካፈሉበት ጊዜ ብቃታቸው በጸጋው ብቻ መሆኑን በመገመትና በትህትና፣ ራስን በመመርመርና በመናዘዝ፤ የጌታን ሞትና የሰጠንን ደኅንነት በማሰብና በባለውለታነት፤ ዳግመኛ እንደሚመጣ በማሰብና በባለተስፋነት ከሞቱም የተነሳ ከሌሎች ጋር ስላለን ኅብረት በመደሰት፤ ለሌሎችም ሞቱን ለመናገር በመዘጋጀት መሆን ይገባዋል።

www.holisticbiblecollege.org

### የጌታ እራት በሚወሰድበት ጊዜ ምን እናስብ?

የጌታ እራት በሚወሰድበት መታሰብ የሚገባቸው ሶስት ዋና ዋና ነገሮች።

1. **የአዲስ ኪዳን መታሰቢያ ነው**



- *"ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና፤ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም፦ እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ <u>ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።"</u>* (1ኛ ቆሮ 11፡23-24)
- የጌታን መከራና ሞት ወይም የአዲስ ኪዳን ማስታወሻ ነው። ጌታችን ስለ ሰው ልጆች ሲል በመስቀል ላይ መሞቱን፣ መነሳቱንና ወደ ሰማይ ማረጉን የምናስታውስበት ነው። (ሉቃ 22፡20 1ኛ ቆሮ 11፡26)

- ከጌታና ከአማኞች ጋር ያለን ሕብረት መሰረቱ የመስቀል ስራ እንደሆነ እንድናስብና (1ኛ ቆሮ 10፡17)።
- የጌታ እራት ምሳሌያዊ ማብራሪያ፡- ለምሳሌ አንድ ወንድማችን ፎቶግራፉን ቢሰጠንና ይህ እኔ ነኝ ይህን ለማስተወሻ ውሰዱት ቢለን ፎቶግራፉ በራሱ ግን ልጁ ራሱ አለመሆኑን እናውቃለን፡፡ ነገር ግን ለወንድማችን ባለን አክብሮትና ፍቅር መጠን ለፎቶግራፉ ያለን አክብሮት ይወሰናል፡፡ ለፎቶግራፉ ያለን አክብሮትና ፍቅር መጠን ለፎቶግራፉ ያለን ከበረታ ከጠፋ ለወንድማችን ያለንን ጥላቻ ገለጽን ማለት ነው። ልክ እንዲሁ የጌታ እራትም የጌታ ሥጋና ደም ምሳሌያዊ ነው።

## 2. የቤተክርስቲያን አንድነት መገለጫ

- *"አንድ እንጀራ ስለ ሆነ፥ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና።"* (1ኛ ቆሮ 10፡17)

## 3. ዳግም ምጽዓቱን የምናስታውስበት ነው

- የጌታ እራት ስንቀበል ወደፊት ሊሆን ያለውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የምናስታውስበት ነው(1ኛ ቆሮ 11፡26)።

## የጌታ እራት ከምን ይዘጋጅ?

የመታሰብያነቱ ቁም ነገር የሙብሉና የመጠጡ ዓይነት ላይ ሳይሆን ድርጊቱ ላይ ስለሆነ የግድ ህብስትና ወይን መሆን የለበትም።

የአማኞች አንድነትና አንድ ሥጋ ለሁሉም መቆረሱን የሚያመለክት ለመሆኑ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 10 ላይ ገልፆታል። የጌታን ደም የሚወክለው ደግሞ ማንኛውንም ከአልኮል ነፃ የሆነ ማንኛውም የሚጠጣ ነገር መጠቀም ይቻላል።

ስለዚህ የጌታ ስጋ የሚወክለው በአካባቢው የሚገኝ እህል በመጠቀም እርሾ የሌለበትን አንድ ቂጣ ቢሆን ይመረጣል። ይህንን የሚያዘጋጀው አማኙ በራሱ ሳይሆን ቤተክርስቲያን ናት።

## ስርአቱን በመስጠት ማን ያገልግል

የጌታን እራት በመስጠት ወይም ማካፈል የተገባቸው እነማን ናቸው ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ የመፍትሔ ሀሳቦች ይሰነዝራሉ። ይህም ለመስጠት ሆነ አገልግሎቱን አስመልክቶ ለመጸለይ የተለየ ሹመትና ሥልጣን ያላቸው ሰዎች ያስፈልጋሉ ወይስ ማንኛውም ክርስቲያን ወይም

www.holisticbiblecollege.org

የተወከለ ሁሉ አገልጋይ ማድረግ ይችላል? ይህንን አስመልክቶ ሁለት ጉልህ አመለካከቶች/Views አሉ።

- ✓ የጌታ እራትንም ሆነ ሌሎችን ተመሳሳይ ሥርዓቶች ማድረግ የደህንነትን ጸጋ መቀበያ መንገድ ነው የሚሉት ወገኖች ስርዓቱን የሚያስፈጽመው ጳጳሱ፣ ካህኑና ልዩ ሹመት የተሰጠው ብቻ መሆን አለበት። ምክንያቱም ስርዓቱ ይህ ሥልጣን በሌላው ሰው ቢከናወን የጌታን ሥጋና ደም አይወክልም ብለው ስለሚያምኑ ነው።
- ✓ የጌታ እራት ሥርዓት መታሰቢያ ነው ብለው በሚያምኑቱ ዘንድ ማንኛውም በሥርዓቱ ለመካፈል የተገባው ሰው ሁሉ በሥርዓቱ ለመካፈል የተገባው ሁሉ ሥርዓቱንም ማስፈጸም ይችላል ብለው ያምናሉ።

## <u>የጌታ እራት ከመካፈል የሚያግዱ ነገሮች?</u>

*"ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ <u>ሳይገባው</u>/unworthily የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል። ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፤ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር እንዳንኮነን በጌታ እንገሠጻለን። ስለዚህ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ ለመብላት በተሰበሰባችሁ ጊዜ እርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ። ማንም የራበው ቢኖር ለፍርድ እንዳትሰበሰቡ በቤቱ ይብላ። የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ።"* (1ኛ ቆሮ 11:28-34)

www.holisticbiblecollege.org

የጌታ እራት ሊካፈል የሚገባ ሰው:-

- ✓ ስለ ጌታ እራት ምንነት በደንብ የተረዳ፤
- ✓ የውኃ ጥምቀት ወስዶ የቤተክርስቲያን አባል የሆነ፤
- ✓ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከሚከሰው ማንኛውም ኃጢአት ራሱን በንስሃ ያነጻ፤
- ✓ በድፍረት ኃጢአት ውስጥ የማይመላለስ፤

የጌታ ከመካፍል የሚያግደው ከእርሾ አለመጠበቅ ነው(ዘጸ 12:14-20)። በአዲስ ኪዳን የእርሾ ትርጉም:-

- ✓ የኑፋቄ ትምህርት መከተል(ማቴ 16:6/12)፤
- ✓ የተገለጡ ኃጢአቶች(1ኛ ቆሮ 5:11-13)፤
- ✓ እግዚአብሔርን ወይም ወንድሙን በቤተክርስቲያን ፊት የበደለ።

- አማኞች ሁሉ የጌታ እራት የመካፈል መብት አላቸው። የጌታ እራት የሚካፈሉ አማኞች ሁሉ የተገባቸውና የገባቸው ሊሆኑ ያስፈልጋል (1ኛ ቆሮ 11፡27-32)።
- የተገባቸው ማለት የዳኑና (ደህንነትን ያገኙ) በተጨማሪም በዚያ ጊዜ ከጌታም ሆነ ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጤናማ የሆነ ማለት ነው።
- የገባቸው ማለት ደግሞ የጌታ እራት ምንነቱን የተረዱ ማለት ነው። ያለ አግባብ የጌታን እራት መካፈል ድካምን፣ ህመምን፣ ስጋዊ ሞትን ፍርድንና ኩነኔንም ያስከትላል።
- ክርስቲያኖች የጌታን እራት በሚካፈሉበት ጊዜ ብቃታቸው በጸጋው ብቻ መሆኑን በማሰብና በትህትና፣ ራስን በመመርመርና በመናዘዝ፣ የጌታን ሞትና የሰጠንን ደኅንነት በማሰብ፣ በመደሰት፣ ለሌሎችም ሞቱን ለመናገር በመዘጋጀት መሆን ይገባዋል።
- ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት ሌሊት ለደቀመዛሙቱ ሞቱን ለማሳሰብ ህብስትና ወይን በመስጠት ሲሆን *"ይህንን ለመታሰብያዬ አድርጉት"* በማለት ነግሯቸዋል። ጌታ ኢየሱስ *"መታሰብያዬ"* ሲል አማኞች ይህንን ስርዓት ሲወስዱ ማሰብ የሚገባቸው ነገር መኖሩን ያመለክታል።
- ሕብስቱ የኃጢአት መስዋዕት ለመሆን ብቃት ያለውንና ፍጹም የሆነውን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ የሚወክል ሲሆን ወይን ደግሞ ለኃጢአት ስርየት የፈሰሰውን ደሙን ያመለክታል። ስለዚህ የጌታ እራት ሲወሰድ ጌታ በመስቀል ላይ የፈጸመውን ስራና ትንሳኤውን እንዲሁም በደሙ የተደረገውን ኪዳን በማሰብ መሆን አለበት።

<u>**የጌታ እራት በየስንት ጊዜ ይፈጸም?**</u>

*"በኢየሩሳሌም በነበረችው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አማኞች ይህን ስርዓት በኅብረት ያደርጉ ነበር"* (ሐዋ 2፡42)።

*"ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን፥ ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ስላሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፥ እስከ መንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አስረዘመ።"* (ሐዋ 20፡7)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጌታ እራት በየስንት ጊዜ መወሰድ እንዳለበት የሚገልፅ ክፍል አናገኝም። ተገቢ በመሰለን ጊዜ በቤተክርስቲያን መሪዎች ተዘጋጅቶ ሊወሰድ ይችላል።

ስለዚህ አማኞች ለመታሰቢያነት ሳያቋርጡ እንዲጠቀሙበት የተሰጠ ስርዓት መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአግባቡና በበቂ እውቀት ሆነው መፅመናን ቢፈጽሙት ይመረጣል።

# 3.3 ልዩ ልዩ ስርዓቶች

የቤተክርስቲያን ዋና ዋና ስርዓቶች ሁለት ናቸው። እነሱም የውሃ ጥምቀት እና የጌታ እራት ሲሆኑ ሌሎች ልዩ ልዩ ስርዓቶችም ቤተክርስቲያን ታስፈጽማለች።

## 1. የጋብቻ ስርዓት

ጋብቻ እግዚአብሔር በራሱ ተነሳሽነት ለሰው ልጆች ያዘጋጀው ቀዳሚ ተቋም ሲሆን መጀመርያዎቹ ተጋቢዎች አዳምና ሄዋን ነበሩ (ዘፍ 2፡20-22)።

በአዲስ ኪዳን ጋብቻ እግዚአብሔርን መንግሥት ቤተክርስቲያን ልታጋባ ይገባል። ቤተክርስቲያን እውና ስትሰጥ በመንፈሳዊው ዓለም የጋብቻው ትክክለኛነት በእግዚአብሔር ዘንድ ይረጋገጣል። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ወንድና ሴት አማኝ ጥንዶችን ታጋባለች።

## 2. ልጅን ለጌታ የመስጠት ስርዓት

ልጆች ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚሰጡ በረከቶች ሲሆኑ (መዝ 127፡3) በስነ-ስርዓትና በእግዚአብሔር ቃል ማሳደግ የወላጆች ቀዳሚ ኃላፊነት ሆኖ እናገኘዋለን (ዘዳ 4፡9፣ 6፡7፣ ምሳ 22፡6)።

ልጆችን ለጌታ የመስጠት ስርዓት አስላፈጊነት፡-

- ወላጆች ከጌታ የተቀበሉትን ልጅ በእግዚአብሔር ቃል፣ በስነ-ስርዓት እንዲሁም በጤናና በትምህርት ተንከባክበው እንደሚገባ ለማሳደግ በእግዚአብሔርና በምዕመናኑ ፊት ቃል የሚገቡበት ጊዜ ነው።
- ልጆች የእግዚአብሔር ምህረት፣ ፀጋ፣ ጥበቃና የሚያፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ጌታ እንዲያዘጋጅላቸው እንዲሁም በዘመናቸው ሁሉ እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲኖሩ ለጌታ የመስጠት ጊዜ ነው።

ስለዚህ ወላጆች የቤተክርስቲያን መሪዎች ባዘጋጁላቸው መሰረት ልጆቻቸውን ለጌታ የመስጠት ስርዓት መፈፀም ይኖርባቸዋል።

## 3. የቀብር ስርዓት ማስፈጸም (ሐዋ 8፡2)

አማኞች በምድር ላይ መቆየት ያለባቸውን ዕድሜ ፈጽመው ወደ ጌታ ሲሰበሰቡ ምንም እንኳ ከጌታ ጋር ለመኖር የሚያልፉት መስመር ቢሆንም (ፊል 1፡21-24) እግዚአብሔር ለአዳም አፈር

www.holisticbiblecollege.org

ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ እንዳለው ሁሉ ስጋው በምድር ውስጥ ማገፍ ስላለበት ቤተክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓት መፈፀም ይጠበቅባታል።

ምንም እንኳ የሟች ቤተሰቦች ወዳጃቸው ከመለየቱ የተነሳ አዝነው ቢያለቅሱም በቀብሩ ስርዓት የተገኘው ሕዝብ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ ማድረግ እንዲሁም መዝሙር በመዘመር እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ ማድረግ ተገቢ ነው። ይሁን እንጂ እንዳያለቅሱ መከልከል ተገቢ አይሆንም።

## 4. ለአገልግሎት ሰዎችን መለየት ስርዓት

*“እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፦ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ። በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው።”* (ሐዋ 13፡2-3)

በአምስቱ የአገልግሎት ሥጦታ እግዚአብሔር የጠራቸውን፣ ስጦታቸውን አይታ እውቅና ሰጥታ ትለያለች። ቤተክርስቲያን ትለያለች እንጂ አትሾምም።

www.holisticbiblecollege.org

# ማጠቃለያ

- ጥምቀት የሚለው ቃል "ባፕቲዞ" ከሚል የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጓሜው መስጠም ወይም መሸፈን ማለት ነው። ሌላው ትርጓሜው ደግሞ በአንድ ነገር ተጽዕኖ ስር መሆን ማለት ነው።
- የጥምቀት ዓይነቶች፡-
  - ✓ የአይሁድ ጥምቀት
  - ✓ የዮሐንስ ጥምቀት
  - ✓ የመከራ ጥምቀት
  - ✓ ወደ ክርስቶስ መጠመቅ(የአካሉ ጥምቀት)
  - ✓ የውኃ ጥምቀት
  - ✓ የእሳት ጥምቀት።
- ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ከጥምቀት ቀጥለው ይፈጽሙት ዘንድ በቋሚነት ከሰጣቸው ስርዓቶች ሁለተኛው የጌታ እራት ነው።
- አማኞች ሁሉ የጌታን እራት የመካፈል መብት ቢኖራቸውም የሚካፈሉት ሁሉ ግን የተገባቸውና የገባቸው ሊሆኑ ያስፈልጋል (1ኛ ቆሮ. 11፡27-32)።
- የጋብቻ ስርዓት፣ ልጅን ለጌታ መስጠት ስርዓት፣ ቀብር ስርዓት ማስፈጸም እና የአገልግሎት ጥሪ መለየት ስርዓቶችን ታስፈጽማለች።

www.holisticbiblecollege.org

# የክለሳ ጥያቄ ሦስት

- **እውነት ወይም ውሸት**

1. የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ከክርስቲያን ጥምቀት የቀደመ የብሉይ ኪዳን ጥምቀት ነው።
2. የፋሲካ በዓል ዋና ዓላማ እስራኤል ከግብጽ የመውጣታቸው መታሰቢያ ነው።
3. የእሳት ጥምቀት ፍርድ ነው።
4. አማኞች የሚጠመቁት ለመዳን ነው።
5. የጌታ እራት አማኞች ለመታሰቢያነት ሳያቋርጡ በግል እንዲጠቀሙበት የተሰጠ ስርዓት መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአግባቡና በበቂ እውቀት ሆነው መዕመናን በቤታቸው ሊፈጽሙት ይገባል።

- **ምርጫ**

1. ከሚከተሉት ውስጥ በዚህ ምዕራፍ ያልተዳሰሰው የትኛው ነው?
   **ሀ**) የጌታ እራት
   **ለ**) የውሃ ጥምቀት
   **ሐ**) የቤተክርስቲያን አስተዳደር
   **መ**) ለአገልግሎት ሰዎችን መለየት
2. ከሚከተሉት ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ወዲያውኑ የእግዚአብሔር ልጅነቱ እንዲጸና በመንፈስ ቅዱስ ወደ ሁሉን አቀፍ ቤተክርስቲያን አካል የሚጨመርበት ጥምቀት ነው?
   **ሀ**) የውሃ ጥምቀት
   **ለ**) የአካሉ ጥምቀት
   **ሐ**) የመከራ ጥምቀት
   **መ**) የእሳት ጥምቀት
3. ከሚከተሉት ውስጥ የቤተክርስቲያን ልዩ ልዩ ስርዓት **ያልሆነው** የትኛው ነው።
   **ሀ**) ለአገልግሎት ሰዎችን መለየት
   **ለ**) የጋብቻ ስርዓት
   **ሐ**) የጌታ እራት
   **መ**) የቀብር ስነ ስርዓት መፈጸም
4. ከሚከተሉት ስለ ጌታ እራት **ውሸት** ነው
   **ሀ**) የጌታ እራት ለመካፈል የተገባቸው እና የገባቸው ሊሆኑ ይገባል

www.holisticbiblecollege.org

**ለ**) ከጌታ ጋር እራቱን ሲበሉ ጌታ እንደተናገራቸው ስጋው የደሙ፤ ጽዋው ደግሞ የእንጀራው ምሳሌዎች ናቸው።

**ሐ**) ክርስቲያኖች የጌታን እራት በሚካፈሉበት ጊዜ ብቃታቸው በጸጋው ብቻ ማድረግ አለባቸው

**መ**) የጌታ እራት የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌያዊ ነው።

**5.** ከሚከተሉት ውስጥ የጌታ እራት ከመካፈል ይከለክላል

**ሀ**) ከእርሾ አለመጠበቅ

**ለ**) የኑፋቄ ትምህርት መከተል

**ሐ**) የተገለጡ ኃጢአቶች ውስጥ መኖር

**መ**) ሁሉም መልስ ነው

❖ **<u>አጭር መልስ</u>**

1. የጌታ እራት ስርዓት የተጀመረው መቼ ነው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

2. የጌታ እራት ስርዓት መታሰቢያ ብቻ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

3. የጌታ እራት ሲወሰድ መታሰብ የሚገባቸው ዋና ዋና ነገሮች ምን ምን ናቸው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------

4. ያለ አግባብ በጌታ እራት መሳተፍ ምን ጉዳት አለው?

---------------------------------------------------------------------------------------------------

www.holisticbiblecollege.org

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

5. በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የተረዳኸውን ወይም አዲስ ያወከውን አጠር አድርገህ ግለጽ?

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

www.holisticbiblecollege.org

# የክለሳ ጥያቄዎች መልስ

| የክለሳ ጥያቄ አንድ | | የክለሳ ጥያቄ ሁለት | | የክለሳ ጥያቄ ሶስት | |
|---|---|---|---|---|---|
| እውነት ወይም ውሸት | ምርጫ | እውነት ወይም ውሸት | ምርጫ | እውነት ወይም ውሸት | ምርጫ |
| 1. ውሸት | 1. ሀ | 1. ውሸት | 1. ለ | 1. እውነት | 1. ሐ |
| 2. እውነት | 2. ሀ | 2. እውነት | 2. መ | 2. እውነት | 2.ለ |
| 3. እውነት | 3. ለ | 3. እውነት | 3. መ | 3. እውነት | 3.ሐ |
| 4. ውሸት | 4.ሐ | 4. ውሸት | 4.መ | 4. ውሸት | 4.ለ |
| 5. እውነት | 5.ለ | 5. እውነት | 5. ሀ | 5. ውሸት | 5.መ |

www.holisticbiblecollege.org

# ዋቢ መጽሐፍት


- Bruce. F.F Tyndal New Testament Commentry. Michingan: William B. Eerdmans, 1985
- Erickson, Milard, Christaian Theology, Michingan! Backer Book Hous, 1983.
- ዋይን ግሩደም- ስልታዊ ስነመለኮት (1994)
- ቻላቸው መከር (1999)- የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ፤ አሳታሚ የኢትዮጵያ ሙሉ ወንጌል ስነ-መለኮት ኮሌጅ፤ በብራና ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ
- ዋና ዋና የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጦች፣ በሲ.ኤስ.ሉዊስ (ትርጉም ተክሉ መንገሻ)
- Smith, Oswald, Challenges of Missions
- Pate, Larry- Starting New Church


www.holisticbiblecollege.org